

Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)

# ፎል 2023 እንደገና ስለመክፈት መመሪያ

# ማውጫ


የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ደብዳቤ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

ለሁሉም ፍትኃዊነትን ማረጋገጥ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4

የፀረዘረኝነት ሲስተም ኦዲት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5

ባህላዊ ምላሽ መስጠትን ያዳበረ የቤተሰብ ተሳትፎ. . . . . . . . . . . . . 5

ተግባራዊ ሥራዎች፣ አስፈላጊ ትጥቆች እና ደህንነት . . . . . . . . . . . . . . . . . 6

የምግብ እና የስነአመጋገብ አገልግሎት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 7

ጤንነት እና የደህንነት ቅደምተከተል. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8

የሚጠበቁ ነገሮች፡- ስርዓተ ትምህርት እና ማስተማር. . . . . . . . . . . . . . . . 11

ጣልቃ ገብነቶች. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 14

የሚጠበቁ ነገሮች፡- ስፔሻል ኢጁኬሽን. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 15

የሚጠበቁ ነገሮች፡- MCPS ቨርቹዋል አካደሚ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . 17

ውጤት መስጠት፣ ትምህርት ላይ መገኘት፣ መሥራት እና ኃላፊነት/ተጠያቂነት . . . 18

የውጤት አሠጣጥ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .18

ኃላፊነትና ተጠያቂነት. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 18

መገኘትን ሪፖርት ማድረግ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 23

የደህንነት-ቁመና ቡድኖች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 23

ቨርቹወል አካደሚ መገኘት/መከታተል. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .23

ለተማሪዎች፣ ለሰራተኞች እና ለቤተሰቦች ድጋፍ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 24

የማህበረሰብ ተሳትፎ እና ግንኙነት. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 25

ቴክኖሎጂ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 26

ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች እና አትሌቲክስ . . . . . . . . . . . . . . 27

2023-2024 የትምህርት አመት ካላንደር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 28

2023-2024 የኢኖቬቲቭ ስኩል ካላንደር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 29

ግብረመልስ/አስተያየት መስጠት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 30




2023 ፎል የተሐድሶ መመሪያ በየአመቱ እየታተመ የሚሠራበት ሰነድ ነው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና ጥበቃ እና ሰብአዊ አገልግሎት ክፍልን (DHHS) ጨምሮ በባለሙያ ድርጅቶች እና መንግስታዊ ኤጀንሲዎች፣ በሜሪላንድ ስቴት ትምህርት መምሪያ (MSDE) እና በሜሪላንድ የጤና ጥበቃ መምሪያ (MDH)፣ የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከል፣ እና በአሜሪካ የህፃናት ህክምና አካዳሚ መመሪያ ላይ ማሻሻያ በተደረገ ጊዜ ሁሉ፣ ፖሊሲዎች እና አሰራሮች ላይ ለውጦችን ማድረጉ ይቀጥላል።



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

# የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ደብዳቤ

ውድ ወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ ተማሪዎች እና ሰራተኞች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ፎል 2023 እንደገና የሚከፈትበትን መመሪያ ሳካፍላችሁ ደስታ ይሰማኛል። ይህ መመሪያ በዲስትሪክቱ ለሁሉም ተማሪዎች በሳምንት አምስት ቀን በአካል ተገኝተው ስለሚሰጣቸው ትምህርት ቀጣይነት አጠቃላይ ወቅታዊ መረጃ ይዟል። መመሪያው ከስቴት እና ከአካባቢው የጤና ባለስልጣናት ጋር በመተባበር የተወሰነውን የዲስትሪክቱን ወቅታዊ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መመሪያ ጠቅለል አድርጎ ያቀርባል።

ይህ መመሪያ ከዲስትሪክቱ የስትራቴጂክ እቅድ አምዶች ጋር የተጣጣመ ነው:-

- አካዴሚያዊ ልህቀት
- የደህንነት ቁመና የቤተሰብ ተሳትፎ፣ እና
- የሙያ እና ተግባር ልህቀት።

የላቀ የማስተማር አገልግሎት እና ለመማር ምቹ ሁኔታ በማቅረብ ስኬታማ የሆነ የትምህርት ምህዳርን ለመፍጠር የምንሰራው ስራ ላይ በምናደርገው እያንዳንዱ ውሳኔ እነዚህ ግቦች መንፀባረቅ አለባቸው። ይህን ተግባር ተማሪዎቻችን ሲመረቁ ለኮሌጅ፣ ለስራ እና ለማህበረሰብ አገልግሎት በሚያዘጋጃቸው መንገዶች እናራምዳለን።

ተማሪዎች ከፍተኛ የአካዳሚክ አፈጻጸም ደረጃ ላይ እንዲደርሱ እና በተሟላ አቅም መሥራት እንዲችሉ አካላዊ፣ ማህበራዊ እና ስነ ልቦናዊ ድጋፎችን ማግኘት አለባቸው። MCPS ለትምህርት ቤቶች እና በካውንቲው ውስጥ የአዕምሮ ጤና ፕሮግራሞች ተደራሽነትን ጨምሮ የተሻሻለ የስነ-ልቦና አገልግሎቶችን ለመስጠት በዚህ ዙርያ ተጨማሪ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰሱን ይቀጥላል። በወረርሽኙ ወቅት እንዳየነው ተማሪዎች በአካል፣ በአእምሮ እና በመንፈስ ጤናማ ሲሆኑ በትምህርታቸው የተሻለ እንደሚሰሩ እናውቃለን።

በትምህርት ስርአታችን ውስጥ በሙሉ ቁርጠኛ ሰራተኞች ከሌሉ ከነዚህ የትኛውም ሊሣካ  አይችልም - መምህራኖቻችን የትምህርት ስርዓታችን የጀርባ አጥንት ናቸው፣ እና ባለፉት አመታት ውስጥ በነበረው የወረርሽኝ ክስተት ተነሳስተው ለተማሪዎቻችን የሚያደርጉትን እንክብካቤ አሳይተዋል። እንዲሁም የግል ትምህርት ቤቶቻችንን የሚመሩ ባለራዕይ አስተዳዳሪዎች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ለተማሪዎቻችን እና ለማህበረሰቦቻችን ወሳኝ የሆኑ አጠቃላይ አገልግሎቶችን  ድጋፍ ሰጥተዋል።

ኮቪድ-19 ቫይረስ ከዚህ በኋላ የህዝብ ጤና ስጋት ባለመሆኑ እድለኞች ብንሆንም፣ በአካል ትምህርት መስጠታችንን ስንቀጥል በንቃት መጠበቅ አለብን። ሲታመሙ ቤት መቆየት እና የአየር ማናፈሻ/የቤት ውስጥ የአየር ጥራት ማሻሻያዎች ኮቪድ-19 እና ሌሎች የመተንፈሻ አካላት ኢንፌክሽኖችን ለመዋጋት ወሳኝ የጤና ስልቶች ናቸው።

ወረርሽኙ በነበረበት ወቅት በተማርነው ጠንካራ ውጣ ውረድ ምክንያት በመጪው አመት አቅማችንን አጠናክረን ለመቀጠል በጉጉት እንጠባበቃለን።

ከመልካም ወዳጅነት ጋር

Monifa B. McKnight, Ed.D.
ሞኒፋ ቢ. ማክኒት ዶ/ር
Superintendent of Schools
የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential



# ለሁሉም ፍትኃዊነትን ማረጋገጥ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ዋና የፍትሃዊነት መርህ በዲስትሪክቱ ዕቅድ እና ውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ ተካቷል። የሚከተሉት የፍትሀዊነት ጥያቄዎች ለዲስትሪክቱ ዕቅድ ለማዘጋጀት ባደረግናቸው ጥረቶች በማስረጃነት እንደግብአት ጠቅመውናል።

## ይህ ተሞክሮ/ውሳኔ ለማን ያገለግላል ወይስ ማንን ችላ ይላል?

» በተግባር ወይም በውሳኔ የትኞቹ የዘር/ጎሳ ቡድኖች  በአሁኑ ጊዜ  በጣም ተጠቃሚ እና ወይስ በጣም የተጎዱ ናቸው?

» ውሳኔው እነርሱን በተለየ ሁኔታ የሚነካቸው እንዴት ነው?

## በውይይቱ የማን ድምፅ ይበልጥ ተቀባይነት አለው/የጎላ ተፅእኖ ያደርጋል? ወይስ የማን ድምፅ በውይይቱ ተሰሚነት አላገኘም?

» ማን አልተገኘም እና እንዴትስ ሊሳተፉ ይችላሉ?

» የዚህ ተግባር/ውሳኔ አሠራር እንዴት ነው የተገለጸላቸው? ትርጉም ባለው መልኩ ተሳትፈዋል? እና በትክክል በእውነተኛ ተወክለዋል?

## በዚህ ውሳኔ ምክንያት ምን ዓይነት አሉታዊ ተጽዕኖዎች ወይም ያልታሰቡ ውጤቶች ሊከተሉ ይችላሉ?

» የትኞቹ የዘር/የጎሳ ቡድኖች አሉታዊ ተጽዕኖ ሊደርስባቸው ይችላል?

» አሉታዊ ተፅእኖዎችን እንዴት መከላከል እንደሚቻል እና በዘር እኩልነት እና ውጤቶች ላይ አዎንታዊ ተፅእኖዎችን ለማረጋገጥ ምን ድንጋጌዎች ይቀየራሉ ወይም ይታከላሉ?

## ቀጣይነት ያለው የመረጃ አሰባሰብ እና የውጤቶቹ ነፀብራቅ ምን ደረጃዎች አሉት?

» በዚህ ውሳኔ ውስጥ የምንጠቀምባቸው እና የማንጠቀምባቸው የመረጃ-ውሂብ ነጥቦች የትኞቹ ናቸው?

» ውጤቶች እና ጠቀሜታቸው እንዴት በሰነድ ተይዘው ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ይገለጻሉ?

## አፈፃፀሙን እየመሩ ያሉት ባለድርሻ አካላት ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ምን ያህል ስብጥር አላቸው?

» የተለያዩ ማንነቶች እና አመለካከቶች (ዘር፣ ጎሳ፣ ጾታ፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ሚና/አቋም) ተገቢ ውክልና ኖሯቸው የአሠራር ወይም የውሳኔ አፈፃፀምን እንዲያውቁት ይደረጋል?



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# ለሁሉም ፍትኃዊነትን ማረጋገጥ (ቀጣይ)

## የፀረዘረኝነት ሲስተም ኦዲት




ሜይ 11, 2023 በፀረ-ዘረኝነት ስርዓት ላይ መወሰድ ያለበት እርምጃ ለትምህርት ቦርድ እና ለማህበረሰብ ቀርቧል። የድርጊት መርሃ ግብሩ ከህብረተሰቡ አባላት እና ከተለያዩ መስሪያ ቤቶች ጋር በመ ተባበር የተዘጋጀ ነው። ዕቅዱ በኦዲት ምርመራ የተገኙትን ተግባ ራዊ መደረግ ያለባቸው ስድስት ጉልህ ጉዳዮችን ይዘረዝራል። የድር ጊት መርሃ ግብሩ በዚህ በይነ መረብ ላይ ይገኛል፡- https://www2.montgomeryschoolsmd.org/antiracist/action-plan/

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አመራር በፀረ ዘረኝነት አሠራር ላይ ያተኮረ ሙያዊ ትምህርት ላይ በመሳተፍ ግኝቶቹን እና የተሰጡ ምክረሃሳቦችን ተግባራዊ ማድረግ ይቀጥላል። ባለፈው ዓመት ዲስትሪክት አቀፍ-ሰፊ የፀረ-ዘረኝነት ትግበራ ቡድን አቋቁመናል። ይህ 60 አባላት ያሉት ቡድን ተማሪዎችን፣ ሰራተኞችን እና ቤተሰቦችን የሚረዱ መገልገያ ቁሳቁሶችን እና ግብዓቶችን አዘጋጅቷል።

## ባህላዊ ምላሽ የመስጠት ልምድ ያዳበረ የቤተሰብ ተሳትፎ



ሁሉም ርእሰ መምህራን በትምህርት ቤት መሻሻል ሂደት በቤተሰብ እና በማህበረሰብ ተሳትፎ ላይ ያተኮረ የሙያ ሥልጠና አግኝተዋል፤ በተመሳሳይ ወላጆችን እና ተንከባካቢዎችን ለማሳተፍ ስለ ፀረ-ዘረኝነት እና ባህላዊ ብዝሃነት ተገቢ አሠራሮችን የሚመለከት ሪሶርሶች/ግብዓቶች ድጋፍ እና ስልጠና ተሰጥቷቸዋል። እነዚህ መገልገያዎች/ሪሶርሶች የሚያካትቱት፡-

- ውጤታማ የቤተሰብ ተሳትፎ እና ግንኙነትን ለማቀድ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን፣ ሀሳቦችን እና ምሳሌዎችን የሚሰጥ ደረጃ በደረጃ የማቀድ መመሪያ
- በትምህርት ቤት-ማሻሻያ ሂደት ውስጥ ቀጣይነት ያለው የወላጅ ተሳትፎን ለማረጋገጥ ከሚጠበቁ ተግባራት ጋር የሙያዊ እድገት ሞጁሎች
- የተለያዩ ማህበረሰቦችን ለማሳተፍ ግልፅ ግንኙነት ማድረግ/መፃፍ እና የብዝሃነት ባህሎችን የተካኑ ግንኙነቶችን ለማዳበር ድጋፍ መስጠት

በተጨማሪም፣ ቀጣይነት ያለው፣ ለትምህርት ቤት መሪዎች የማህበረሰብ ተሳትፎ ሙያዊ እድገት ስልጠና 2023-2024 በየማህበረሰቡ ፍላጎት ላይ የተመሠረቱ ልዩ ልዩ አማራጮችን ዝርዝር ውስጥ ማስገባት።



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# ክንዋኔዎች፣ መገልገያዎች እና ደህንነት



## የደወል ሰአቶች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶች ለ 2023-2024 የትምህርት ዓመት የቅድመ ወረርሽኙን መደበኛ የደወል ሰዓታቸውን ይጠብቃሉ።

| የክፍል ደረጃ | ጊዜ | የቀናት ርዝመት |
|---|---|---|
| ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 7፡45 a.m.-2፡30 p.m. | 6 ሰአት 45 ደቂቃ |
| መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 8:15 a.m.–3:00 p.m. | 6 ሰአት 45 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት እርከን (Tier) 1 | 9:00 a.m.–3:25 p.m. | 6 ሰአት 25 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት እርከን (Tier) 2 | 9:25 a.m.–3:50 p.m. | 6 ሰአት 25 ደቂቃ |

## የተማሪና ሰራተኞች ደህንነት እና ጥበቃ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በንብረቱ ላይ ለሚገኙ ሰዎች ሁሉ ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ተማሪዎች እና ሰራተኞች የተሻለ ስራ የሚሠሩበት፣ ስኬት የሚያገኙበት እና የሚበለጽጉበት ሰላማዊ ትምህርት ቤቶች እና የስራ ቦታዎችን ለማጎልበት እና ለመጠበቅ ቁርጠኛ ነው። ከበርካታ የማህበረሰብ ባለድርሻ አካላት እና ከጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት ጋር በመተባበር የተማሪዎችን ማህበራዊ-ስሜታዊ እና የጤና ድጋፍ ፍላጎቶችን ለማሟላት አገልግሎት ለመስጠት ስንሰራ በትምህርት ቤቶች ውስጥ የአእምሮ ጤና እና ደህንነት ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳይ ሆኖ ይቀጥላል። ከህግ አስከባሪ አጋሮቻችን፣የማህበረሰብ ተሳትፎ ኦፊሰር (ስራ አስፈፃሚ) ፕሮግራምን ጨምሮ፣ ለተማሪዎቻችን ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አካታች እና አወንታዊ የመማሪያ አካባቢዎችን ማመቻቸት እንቀጥላለን። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስርአት አቀፍ ደህንነት እና የድንገተኛ/አስቸኳይ ሁኔታ አስተዳደር ጽ/ቤት ከትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ተማሪዎች እና ማህበረሰቦች ጋር በሚሰሩት ስራ ለደህንነት እና የአደጋ ጊዜ ዝግጁነት አጽንኦት በመስጠት መሥራቱን ይቀጥላል።

### ተማሪዎችን ደህንነታቸው በተጠበቀ ሁኔታ የማጓጓዝ አገልግሎት

ሁሉም ተማሪዎች ትምህርታዊ ስኬት እና አካዴሚያዊ ልቀት እንዲያገኙ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትራንስፖርት መምሪያ ደህንነቱ የተጠበቀ፣አስተማማኝ እና ፍትሃዊ የሆነ የመጓጓዣ አገልግሎት ለመስጠት ቁርጠኛ ነው።

2023-2024 የትምህርት ዘመን ባለ አቅም መደበኛ የመጓጓዣ አገልግሎት መስመሮች ስራቸውን ይቀጥላሉ። ቤተሰቦች የተመደበላቸውን ትምህርት ቤት የአውቶቡስ መስመሮች እንዲያውቁ ተደርጓል። በተጨማሪ የአውቶቡስ መጓጓዣ መስመሮችን ለማየት ከዝርዝሩ ላይ የፈለጉትን ትምህርት ቤት መርጠው MCPS ድረገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ:- https://www2.montgomeryschoolsmd.org/departments/transportation/busroutes/

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ደህንነቱ የተጠበቀ ወደ ትምህርት ቤት የመጓጓዝ ፕሮግራም፣ https://ww2.montgomeryschoolsmd.org/saferoutes/ በእግር እና በብስክሌት ወደ ትምህርት ቤት ለሚጓዙ ተማሪዎች እንዲሁም በትምህርት ቤት አውቶቡሶች የመጓዝ ደህንነትን ለመጠበቅ፣ በአውቶቡስ ማቆሚያዎች፣ በሚጭኑበት እና በሚያወርዱበት ጊዜ ሁሉ በጣም የተሻሻለ የአውቶቡስ ጉዞ መስጠት ይቀጥላል።

# የምግብ እና የአልሚ ምግብ አገልግሎት



የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የምግብ እና የተመጣጠነ አመጋገብ አገልግሎት ክፍል (DFNS) 2023–2024 የትምህርት ዘመን መደበኛ የምግብ አገልግሎት መስጠት ይቀጥላል።

## ጠቃሚ ማሳሰቢያ

በሜሪላንድ የቅናሽ ዋጋ ምግብ ለማግኘት ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ለቁርስ ወይም ለምሳ ምግብ አይከፍሉም።

## ቁርስ

መደበኛ ዋጋ $1.30

የቅናሽ ዋጋ የማይከፈል

## ምሳ

መደበኛ ዋጋ $2.55 (አንደኛ ደረጃ)
$2.80 (መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ)
በሁሉም ደረጃዎች የቅናሽ ዋጋ፡- ክፍያ የለውም

ለአዲሱ የትምህርት አመት የነጻ እና የቅናሽ ዋጋ የምግብ ስርዓት (FARMS) ማመልከቻ የተሻሻለ ስለሆነ በኦንላይን www.MySchoolApps.com ማመልከት ይቻላል፥ ይህ ተመራጭ የማመልከቻ ዘዴ ነው። ፍላጎት ያላቸው ቤተሰቦች ሁሉ በየትምህርት ዓመቱ እንደገና ማመልከት አለባቸው። ሚስጥራዊነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁሉም ልጆች MCPS መታወቂያ ቁጥራቸውን ወይም ባር ኮድ ይጠቀማሉ።

2023–2024 የትምህርት አመት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በማህበረሰቡ ውስጥ ብቁነታቸው ለተረጋገጠላቸው ልጆች (CEP) 57 ትምህርት ቤቶች ውስጥ ነፃ ቁርስ እና ምሳ ይሰጣል። ለተመረጡት ተሳታፊ ትምህርት ቤቶች ተጨማሪ መረጃዎችን እናጋራለን።



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# ጤንነት እና የደህንነት አሰራር



MCPS ለሰራተኞቻችን እና ለተማሪዎቻችን ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጤናማ አካባቢ ለማመቻቸት ቁርጠኛ ነው። የትምህርት ስርዓቱ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ (DHHS)፣ ከሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE)፣ ከሜሪላንድ የጤና መምሪያ (MDH) እና ሌሎች ኤጀንሲዎች ለትምህርት ቤቶቻችን እና ለስራ አካባቢዎቻችን ተፈጻሚ የሚደረጉ መመሪያዎችን ያገኛል።

ኮቪድ-19 እና ሌሎች የመተንፈሻ አካላት ኢንፌክሽኖችን በተመለከተ፣ jMDH እና MSDE በጋራ በሰጡት መመሪያ መሠረት ፐብሊክ ስኩልስ ከአካባቢያቸው የጤና ዲፓርትመንት ጋር እንዲሰሩ ይመከራል የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማእከል (CDC) የክዋኔ መመሪያ (K-12) ትምህርት ቤቶች እና ቀደምት እንክብካቤ እና የትምህርት ፕሮግራሞች የሞንትጎመሪ ካውንቲ (DHHS) የአካባቢ ጤና ጥበቃ ባለስልጣን ስለሆነ በት/ቤቶች ላይ የጤና አገልግሎቶችን ይሰጣል። MCPS ሁሉን አቀፍ፣ ማህበረሰብን መሰረት ያደረገ የፐብሊክ ስኩልስ ተማሪዎቻችንን፣ ቤተሰቦቻቸውን፣ እና የሰራተኞቻችንን ደህንነት ለማረጋገጥ በሕዝብ ጤና ጥበቃ ስትራቴጂ ላይ DHHS ጋር በቅርበት ይሰራል።

የዕለት ተዕለት የመከላከል ስልቶች የጤና አጠባበቅ እና የደህንነት ሥርአታችን መሰረት ናቸው። እነዚህን የጋራ አስተሳሰብ እርምጃዎች ያለማቋረጥ ሲለማመዱት ጤና አጠባበቅን ያበረታታሉ እንዲሁም የበሽታ ስርጭትን ይከላከላሉ። በየአካባቢው የበሽታ ስርጭት አዝማሚያን በመከታተል በመሪያ ክፍሎች፣ በተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ወይም በትምህርት ቤት ደረጃ ተጨማሪ እርምጃዎችን በጊዜያዊነት መተግበር ሊያስፈልግ ይችላል።

## መሠረታዊ የጤና አጠባበቅ ስልቶች

### ክትባት

ትምህርት ቤት ለመግባት የተወሰኑ ክትባቶች ያስፈልጋሉ እነዚህም በስቴት የጤና ዲፓርትመንት የሚወሰን እና በት/ቤት ሰራተኞች ክትትል የሚተገበሩ ናቸው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ብቁ ተማሪዎች እና ሰራተኞች ኮቪድ-19 እና ወቅታዊ የኢንፍሉዌንዛ ክትባቶችን ጨምሮ ማናቸውንም ተላላፊ በሽታዎችን የሚከላከሉ ሁሉንም CDC የሚያዛቸውን ክትባቶች በወቅታዊነት እንዲተገበሩ በጥብቅ ይመከራል።

### ጤናማ ልማዶች

ጥሩ የእጅ ንፅህና እና የአተነፋፈስ ስነምግባር የመተንፈሻ አካላት እና ሌሎች የኢንፌክሽን ዓይነቶችን ለመከላከል ይረዳል። ዓመቱን ሙሉ በተለይም ከምግብ በፊት እና በኋላ ባሉት ጊዜያት፣ ወይም መጸዳጃ ቤት ከተጠቀሙ በኋላ አዘውትሮ እጅ መታጠብ ይደገፋል/ይጠናከራል። ትምህርት ቤቶች በቂ የእጅ መታጠቢያ ዕቃዎችን ያዘጋጃሉ እና ከተዋስያን የእጅ ማጽጃ ሳኒታይዘሮችን በስትራቴጂካዊ ቦታዎች ላይ ያስቀምጣሉ። "የመተንፈስ ሥርአት" ማለት በሚያስነጥስበት እና በሚያስሉበት ጊዜ አፍ እና አፍንጫን በመሃረብ ወይም በሚመስል ነገር መሸፈን እና የተጠቀሙበትን ወዲያውኑ ወደ ቆሻሻ ማስወገጃ መጣል እና እጅን መታጠብ ማለት ነው። መሃረብ ወይም ከለስላሳ ወረቀት የተሠራ ነገር የማይገኝ ከሆነ የእጅን መዳፍ ከመጠቀም ይልቅ ወደ እጅጌው ወይም ወደ ክርንዎ ተጠማዞ ማሳል ይሻላል።

### ሲታመሙ ቤት መቆየት

ሲታመሙ ቤት መቆየት ሰውነት እንዲያገግም እና በሽታ ወደሌሎች ሰዎች እንዳይዛመት ይከላከላል። ተማሪዎች፣ ሰራተኞች፣ በጎ ፈቃደኞች እና የታመሙ ጎብኝዎች ከታመሙ ቤታቸው መቅረት አለባቸው። ወይም በትምህርት ቤት ህንፃ ውስጥ እያሉ የሕመም ምልክቶች ከታዩባቸው ህንጻውን ለቀው ለማረፍ ወይም የህክምና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ያስፈልጋል። የአጣዳፊ ሕመም ምልክቶች ትኩሳት፣ ተደጋጋሚ ተቅማጥ ወይም ትውከት፣ ወይም ከባድ የመተንፈስ ችግር፣ ወይም ሌሎች የመሥራት ወይም የመማር ችሎታን የሚያዳክሙ ምልክቶች ናቸው። ለተወሰኑ ኢንፌክሽኖች (ለምሳሌ፣ የጭንቅላት ቅማል፣ የዶሮ ፐክስ፣ የስትሮፕስ ጉሮሮ) የአካባቢ እና የስቴት የጤና መምሪያዎች ወደ ትምህርት ቤት መቼ እንደሚመለሱ የተለየ መመሪያ ሊሰጡ ይችላሉ።

### ጽዳት

የሕንፃ አገልግሎት ሠራተኞች የበር መክፈቻ እጀታዎች፣ የእቃ ማጠቢያ እጀታዎች እና ሌሎች በተደጋጋሚ የሚነካኩ ንጣፎችን በማሳሰሉት ከፍተኛ ንክኪ ያላቸውን መገልገያ ቦታዎች ላይ የበለጠ ትኩረት በመስጠት ትምህርት ቤቶችን እና የስራ ቦታዎችን ስለማፅዳት እና ስለመከላከል የተሰጣቸውን ፕሮቶኮሎች መተግበር ይቀጥላሉ። ተማሪዎች ፀረ-ተባይ መገልገያዎችን ወይም ሌሎች ለሰራተኞች አገልግሎት ብቻ የሚጠቀሙባቸውን አደገኛ የጽዳት እቃዎችን እንዲይዙ አይፈቀድላቸውም። ያልተፈቀዱ የቤት ማጽጃ ምርቶች MCPS ህንፃዎች ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም።



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# ጤንነት እና ደህንነት (ቀጣይ)



## የአየር ማናፈሻ እና የቤት ውስጥ አየር ጥራት

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለጤና እና ለደህንነት ተስማሚ የአየር ማናፈሻ እና የቤት ውስጥ የአየር ጥራትን ለመጠበቅ "American Society of Heating, Refrigeration and Air-Conditioning Engineers (ASHRAE)፣ CDC፣ እና U.S. Environmental Protection Agency (EPA)የተሰጡ መመሪያዎችን ይከተላል። የተወሰዱት እርምጃዎች ሁሉንም የትምህርት ቤት HVAC የአየር ማጣሪያ ሲስተም  ግምገማ፣ HVAC ማጣሪያዎችን ማሻሻል እና መተካት፣ HVAC ክፍት ሆኖ የሚሠራበትን ሠዓት ማራዘም እና ተንቀሳቃሽ የአየር ማጣሪያዎችን አስፈላጊ ቦታዎች ላይ መትከልን ያካትታሉ። የበለጠ መረጃ ስለ እነዚህ በመካሄድ ላይ የሚገኙ እርምጃዎች MCPS የቤት ውስጥ የአየር ጥራት ተቆጣጣሪ ቡድን ተጨማሪ መረጃ MCPS ድረ ገጽ ላይ ይገኛል።

# የበሽታ ስርጭትን ለመከላከል ተጨማሪ እርምጃዎች

## ፊት መሸፈን

MSDE፣ በአከባቢው የትምህርት ቤቶች ዲስትሪክቶች ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ በአካል መማር እንዲችሉ በትክክል የሚገጥም የፊት ጭምብሎችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ሊወስኑ ይችላሉ። በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)፣ በትምህርት ቤት ለታመሙ ወይም በትንሹ 5-ቀን ራሳቸውን አግልለው ከቆዩ በኋላ ለሚመለሱ ግለሰቦች CDC COVID-19 ባስተላለፈው ራስን የማግለል መመሪያ ላይ ከሚጠይቀው ሁኔታ በስተቀር ጭምብል መጠቀም በራስ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነው። በአካባቢ በሚከሰት የአተነፋፈስ በሽታ ምክንያት በጊዜያዊነት ጭምብል መጠቀም ሊመከር ወይም ሊያስፈልግ ይችላል። የጤና አጠባበቅ ክፍሎች እና የትምህርት ቤት የጤና ክሊኒኮች DHHS የደነገገላቸው የተለያዩ መስፈርቶች ሊኖራቸው ይችላል። በህብረተሰቡ ውስጥ ሊከሰት የሚችል የመተንፈሻ አካላት በሽታ ምንም ቢሆን፣ግለሰቦች የራሳቸውን ወይም የሌሎችን ጤና ለመጠበቅ በፍቃደኝነት ጭንብል ቢጠቀሙ ይደገፋል። በወጣትነት ዕድሜ ምክንያት ወይም በጤና እክል ምክንያት ግለሰቦች ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ጭምብል ማድረግ በማይችሉበት ጊዜ አማራጭ ወይም ተጨማሪ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ይመከራል።

## ወረርሽኝ ሲከሰት የሚወሰዱ እርምጃዎች

MCPS እና የት/ቤት ጤና አገልግሎት ሰራተኞች በትምህርት ቤት ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ተላላፊ በሽታዎችን ይቆጣጠራሉ፣ ይኼውም የክትትል መረጃ በመሰብሰብ፣ በአካባቢው የተላላፊ በሽታ አዝማሚያዎችን በመከታተል እና የህዝብ ጤና አጠባበቅ መመሪያዎችን በመተግበር ይከናወናል። ወረርሽኝ መኖሩ ከተረጋገጠ፣ ትምህርት ቤቶች አዳዲስ ኬዞችን ለመቆጣጠር እና ለመለየት፣ የወረርሽኙን ተጨማሪ ስርጭት ለመከላከል እና የጤና መረጃዎችን ለሰራተኞች እና ለቤተሰቦች ለማስተላለፍ እርምጃዎችን ለመተግበር DHS የሚሰጠውን መመሪያ ይከተላሉ።




Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# ጤንነት እና ደህንነት (ቀጣይ.)

## ኮቪድ-19 ምላሽ

በተለይ ስለ ኮቪድ-19 መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች ከዚህ በታች ተገልፀዋል። ተጨማሪ መረጃ MCPS እና ሞንትጎመሪ ካውንቲ ኮቪድ-19 የመረጃ ቋት ላይ ይገኛል።

### ቤት ውስጥ ምርመራ ለማድረግ ጠቃሚ መሣሪያዎች

እንደየአካባቢው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ስርጭት አዝማሚያ እየታየ እቤት ውስጥ የኮቪድ-19 መመርመሪያ መሣሪያ በመጠቀም ማጣራት በአንዳንድ ሁኔታዎች ሊያስፈልግ ወይም ሊመከር ይችላል። ይኼውም በትምህርት ቤት የተከሰተ ወረርሽኝ፣ በትምህርት ቤት ስፖንሰር የተደረጉ የአዳር ጉዞዎች ወይም ከታቀደው ዕረፍት ከመመለሳቸው በፊት ተመርምሮ ማጣራትን ያካትታሉ። እንደነዚህ አይነት ሁኔታዎች ላይ፣ ትምህርት ቤቶች እና የስራ ቦታዎች የመመርመሪያ መሣሪያዎችን ያሰራጫሉ እና የምርመራ ውጤቶችንም ሪፖርት እንዲደረግላቸው ይጠብቃሉ።

### በትምህርት ቤት ወይም ሥራ ቦታ ሊታዩ የሚችሉ የኮቪድ-19 ምልክቶች

በትምህርት ቤት የኮቪድ-19 ምልክት ያለባቸው ተማሪዎች ከአሁን በኋላ በጤና ክፍሎች ውስጥ በመደበኛነት ምርመራ አይደረግላቸውም። የጤና ክፍል ሰራተኞች እንደሁኔታው የቤት ውስጥ መመርመሪያ መሣሪያዎችን ማከፋፈል ይችላሉ። መለስተኛ ምልክት ያለባቸው ሰራተኞች/ተማሪዎች ለቀሪው የትምህርት ቀን ጭምብል እንዲያደርጉ ሊጠየቁ ይችላሉ። ትኩሳት ወይም ከባድ ምልክቶች ኖሯቸው ከትምህርት ቤት ወይም ከሥራ ቦታ የሚሄዱ ግለሰቦች ሕንፃውን ለቀው እስኪወጡ ድረስ ጭምብል እንዲጠቀሙ ይጠየቃሉ።

### በተማሪዎች ወይም በሰራተኞች ላይ በምርመራ የተረጋገጠ ኮቪድ-19 በሽታ

ተማሪዎች ወይም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ኮቪድ-19 ከተያዘ(ች)፣ CDC በሰጠው መመሪያ መሰረት ራስን ማግለል እና ጭምብል የመጠቀም ቅድመ ጥንቃቄዎችን መከተል አለባቸው፣ ይህም በአሁኑ ጊዜ ቢያንስ 5 ቀናት በቤት ውስጥ መቆየትን ያካትታል። ከትምህርት ቤት ወይም ከስራ መቅረትን ሪፖርት ለማድረግ የአካባቢውን ሥርአት መከተል እና የመቅረቱ መንስኤ በኮቪድ-19 ምክንያት መሆኑን መግለጽ ያስፈልጋል። ሰራተኞች እና ተማሪዎች ከአሁን በኋላ ስለ በሽታው/ኬዞችን ለ MCPS በኦንላይን ሪፖርት ማድረግ አይጠበቅባቸውም።

### ለኮቪድ-19 መጋለጥ

ምንም ምልክት ከሌለባቸው እና ስለ ተጋለጡ ሰዎች ሌሎች CDC የሚሰጣቸውን ምክሮች መከተል ከቻሉ፥ ኮቪድ-19 ለተያዘ(ች) ሰው የተጋለጡ ግለሰቦች ራሳቸውን ማግለል አይጠበቅባቸውም። የሰራተኞች እና የተማሪዎች ቤተሰቦች በክፍላቸው ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት ወረርሽኝ ከተከሰተ እና ኮቪድ-19 የመጋለጥ እድላቸው ከፍ ያለ ከሆነ ማሳወቂያ ይደርሳቸዋል። ይህ ማሳወቂያ ተጨማሪ የአካባቢ ኢንፌክሽን እንዳይሰራጭ ለመከላከል የሚያስፈልጉትን ማንኛውንም ጊዜያዊ እርምጃዎችን የሚያካትት ሲሆን ለምሳሌ፡- ጭምብል ማድረግ፣ ምርመራ ማድረግ ወይም ወደሌሎች ሰዎች እንዳይተላለፍ እንቅስቃሴዎችን መገደብ።

### የኮቪድ-19 ወረርሽኝ እና የንክኪ ዱካ ፍለጋ

MCPS የወረርሽኙን ሁኔታ ክትትል ለማድረግ እና የአካባቢ እና የስቴት የህዝብ ጤና ጥበቃ መመሪያዎችን በመከተል የኮቪድ-19 ወረርሽኝን በትምህርት ቤቶች ለመቆጣጠር እና ሪፖርት ለማድረግ ከጤና ጥበቃ እና ሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት (DHHS) ጋር በመተባበር ይሰራል። ለእያንዳንዱ በበሽታ የመያዝ ሁኔታ ወይም ለኮቪድ-19 ወረርሽኝ የመጋለጥ ዱካ ፍለጋ በመደበኛነት አይካሄድም። ወረርሽኙ ከተጠረጠረ፣ MCPS ኬዙን እና የተጋላጭነት መረጃውን ወደ DHHS ያስተላልፋል። ይህ አስፈላጊ መረጃ በሚስጥር የሚጠበቅ ስለሆነ የጤና ክፍል በሚወስነው መሰረት ተጋላጭ የሆኑ ሰዎችን ፍለጋ ሊያገለግል ይችላል።


Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# የሚጠበቁ ነገሮች፡- ስርአተ ትምህርት እና ማስተማር



## ለስኬታማ ማስተማር ማቀድ

የ MCPS ዋና ዓላማ ሁሉም ተማሪዎች በወደፊት ሕይወታቸው እንዲበለጽጉ የሚያግዝ ጠንካራ የትምህርት ፕሮግራም መስጠት ነው። 2023-2024 የትምህርት አመት፣ ሁሉም ተማሪዎች ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲሰሩ ለማድረግ MCPS የትምህርት ቀናት መቆራረጥን መከላከል/ማካካስ እና የድጋፍ እቅዶችን መተግበሩን ይቀጥላል። ዲስትሪክቱ ሁሉም ተማሪዎች ተደራሽነት እንዲኖራቸው እና ማንኛውም በወረርሽኙ ምክንያት የተስተጓጎለባቸውን ትምህርት ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ የብዙ ዓመት ዕቅዶችን አዘጋጅቷል። መመሪያ፣ ድጋፍና የሙያ ትምህርት መምህራን ተማሪዎች ያመለጧቸውን ትምህርቶች ወይም በጣም ባጠረ ሁኔታ የተማሩት ትምህርት ላይ በማተኮር ጠንካራ መሠረት እንዲገነቡ ያስችላቸዋል። መምህራን ትምህርቶችን ሲያቅዱ፣ ከቅድመ-መዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍሎች ሜሪላንድ ለኮሌጅ እና የሙያ ዝግጁነት ደረጃ (MCCRS) እና ከስቴት ደረጃዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ ዋና ዋና የተማሪ ፍላጎቶችን በማመቻቸት ላይ ያተኩራሉ።

በአንደኛ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች  የማስጠናት ጣልቃ ገብ ድጋፍ የሚሰጥባቸው ጊዜያት በትምህርት መርሃ ግብሮች ውስጥ ተካቷል።

### ሒሳብ የማገገሚያ ዕቅድ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሂሳብ ፕሮግራም በሁሉ ደረጃዎች ያሉ ተማሪዎችን ጠንክረው እንዲሠሩ ለማስቻል የተቀየሰ ነው። አላማው ተማሪዎች 7ኛ፣ 8ኛ ወይም 9ኛ ክፍል እየተማሩ አልጀብራ 1 በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለከፍተኛ ደረጃ የሒሳብ ትምህርት Advanced Placement (AP) እና International Baccalaureate (IB) ክፍሎች ጭምር እንዲዘጋጁ ማድረ ነው። በወረርሽኙ ምክንያት የተስተጓጎሉ/ያመለጧቸውን ትምህርቶች ለማካ በእቅዱ ላይ ማስተካከያዎች እየተደረጉ ነው።

የሂሳብ ትምህርት ማገገሚያ ዕቅድ መመሪያ መርሆዎች ምንድናቸው?

- በየሳምንቱ አምስት ቀናት የሂሳብ ትምህርት ይሰጣል።
- ተማሪዎች ያሉበትን የክፍል ደረጃ በሚመጥን ትምህርት ላይ ይሳተፋሉ
- መማር በትምህርቱ ዋና ሥራ ላይ እና የኋላ ድጋፍ/ተጨማሪ ሥራዎች ላይ ያተኩራል።

እቅዱን ለማየት፣ እባክዎ<u>እዚህ ክሊክ ያድርጉ</u>።

### የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ የሊተርሲ ማገገሚያ እቅዶች

» <u>የመጀመሪያ ደረጃ ELA እቅድ</u>

» <u>የሁለተኛ ደረጃ ELA እቅድ</u>

### ሥርዓተ ትምህርትና ለኮሌጅ እና ለሥራ ዝግጁነት

» <u>ሥርአተ ትምህርት</u>

» <u>የሙያ ዝግጁነት</u>

» <u>ጣምራ ምዝገባ</u>

# የሚጠበቁ ነገሮች፡- ሥርዓተ ትምህርት እና ማስተማር (ቀጣይ)



## የማስተማር ግብረመልስ ዕቅድ

በወረርሽኙ ምክንያት ያመለጡ ትምህርቶችን ለማካካስ MCPS የማስተማር ግብረመልስ እቅድ መተግበሩን ይቀጥላል። ምንም እንኳን በአንዳንድ አካባቢዎች እድገቱ የተስተካከለ ባይሆንም የአፈጻጸም መረጃዎች እንደሚያመለክቱት እድገት እና መሻሻል ታይቷል። የታየው መረጃ:-

- 3ኛ፣ 6ኛ እና 9ኛ ክፍሎች በአካል ተመልሰው መማር ከጀመሩ ወዲህ በሊተርሲ ትምህርት የንባብ እድገትና መሻሻል ታይቷል።
- የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች እና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ጨምሮ በተለያዩ ቡድኖች ውስጥ የማንበብ እና መፃፍ መሻሻሎች አሉ።
- በሂሳብ ትምህርት ላይ፣ በተለይም 6ኛ እና 9ኛ ክፍሎች ላይ የነበረው መሻሻል እኩል አልነበረም
- 3ኛ ክፍል ተማሪዎች በሂሳብ ትምህርት ላይ መሻሻል ያሳዩት መሰረታዊ 3ኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርት መማር ላይ ነው።
- በሁሉም ትንሽ እድሜ ላይ የሚገኙ ተማሪዎቻችን ማንበብ እና መፃፍ ክህሎቶች ላይ አሻሽለዋል ግን አሁንም ክፍተቶች አሉ

የማስተማር ግብረመልስ ዕቅዳችን አካል የሆነውን በክፍል ደረጃ ትምህርት ላይ ቀጣይ ትኩረት ለማሳካት፣ እያደረግን ያለነው:-

» ሊተርሲ እና ሂሳብ ትምህርት ላይ ማተኮር

በወረርሽኙ ምክንያት በብዙ ተማሪዎቻችን ዘንድ የነዚህ ትምህርቶች እድገት እንደቀነሰ እናውቃለን፣ ሆኖም ግን ባለፈው የትምህርት አመት እድገት የታየ ቢሆንም፣ በብዙ ተማሪዎች እና የተማሪ ቡድኖች ዘንድ ክፍተቶች እንዳሉ እናውቃለን። ስለሆነም፣ እድገታችንን ለማስቀጠል ከፍተኛ ጥራት ያለው የሊተርሲ እና የሂሳብ ትምህርቶች ላይ እናተኩራለን። በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእንግሊዘኛ ቋንቋ ስነ ጥበብ (ELA)፣ MCPS የሊተርሲ ትምህርት መገንቢያ የሆኑትን ቁልፍ ክህሎቶች ነቅሷል፥ ይሁንና ተጨማሪ ጊዜ በመስጠት ለማስተማር መርሃ ግብሩን አስተካክሏል። አዳዲስ ሪሶርሶች/ግብአቶች እና የሙያ እድገት ስልጠናዎች ት/ቤቶች ተማሪዎቻችንን ለመደገፍ የሚያስፈልጋቸውን እውቀት እና መሳሪያዎችን ይሰጧቸዋል። የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎችን ፍላጎቶች ለማሟላት ከእንግሊዝኛ ቋንቋ መዳበር ስፔሻሊስቶች ጋር መስራትን ጨምሮ በመላው ELA እና በሂሳብ፣ MCPS ሁሉንም ተማሪዎች ለመድረስ ጥረት እያደረገ ነው። በተጨማሪም ተማሪዎች ተቀባይነት እንዲሰማቸው እና በክፍላቸው ውስጥ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለማበረታታት መምህራን በክፍል ውስጥ ጸረ-ዘረኝነትን እና ፀረ-አድሎአዊነትን የማስወገድ ስልቶችን እየተማሩ ነው።

» እንደ አስፈላጊነቱ በክፍል ደረጃ ማስተማር እና ያልተጠናቀቁ ትምህርቶችን ማጠናቀቅ

በክፍል-ደረጃ መሰጠት ያለባቸውን ትምህርቶች እያስተማርን ወደፊት አዳዲስ የትምህርት ምእራፎችን ለመደገፍ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ትምህርት ሁኔታዎችን እየገመገምን እናስተካክላለን። የክፍል ደረጃ ትምህርት እየሰጠናቸው ወደፊት በመጓዝ ተማሪዎችን የበለጠ ወደ ኋላ እንዳይቀሩ መከላከል እንችላለን። መምህራንን እና የት/ቤት መሪዎችን ለመደገፍ የሚያስፈልጉ ጽንሰ-ሀሳቦች እና ክህሎቶች ላይ መመሪያ ሰጥተናል፣ ተገቢ የተማሪዎች የመማር ፍጥነት እየታየ፣ ለበለጠ ትምህርት ዝግጁ ለሆኑት የትምህርት ማበልፀጊያ እድሎችን፣ እና ተጨማሪ ግምገማ እና መመሪያ ለሚፈልጉ ተማሪዎችም ድጋፍ ይሰጣል።

» የተማሪን ትምህርት የመከታተል ሁኔታ ማጤን እና የማስተማር ስልትን ማስተካከል

ሊኖሩ የሚችሉ የእውቀት ክፍተቶችን እየሞላን በክፍል ደረጃ ለማስተማር፣ አስተማሪዎች ተማሪዎቻቸው የሚያውቁትን እና ማድረግ የሚችሉትን መገንዘብ አለባቸው፥ ይሄን መረጃ በመጠቀም በየቀኑ የትምህርት አሰጣጡን ሁኔታ ያስተካክላሉ። ምንም እንኳን በየወቅቱ የሚከናወኑ የትምህርት ምዘናዎች መኖራቸውን ሁላችንም የምናውቀው ቢሆንም፣ የክፍል ፈተናዎች እና የአካዳሚክ ግስጋሴ መመዘኛዎች (MAP) የመሣሰሉት የተማሪዎችን ትምህርት የምንትንመረ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መምህራን በሊተርሲ እና በሂሳብ የግምገማ መሳሪያዎችን በመጠቀም ለማስተማር ያላቸውን አቅም እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል። ይህ ማለት መምህራን ለተማሪዎች ካለፈው አመት ያልተጠናቀቁ ትምህርቶችን መቼ መጨረስ እንደሚፈልጉ እንዲያውቁ የተዘጋጁ ተግባራትን ይሰጧቸዋል፥ እናም የትኞቹ ተማሪዎች ለክፍል ደረጃ ፅንሰ-ሀሳቦች እና ክህሎቶች በመደበኛነት ተጨማሪ ድጋፍ



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# የሚጠበቁ ነገሮች፦ ሥርዓተ ትምህርት እና ማስተማር (ቀጣይ)



እንደሚያስፈልጋቸው ይለያሉ። ይህ ቀጣይነት ያለው ክትትል እና ማስተካከያ ሁሉም ተማሪዎቻችን በሊተርሲ እና በሂሳብ ከክፍል ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ እንዲሰሩ ትምህርቱ በተማሪዎች የመማር ፍላጎት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ያረጋግጣሉ።

» ሁሉም ትምህርት ቤቶቻችን የጋራ ትኩረት እና የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ

በሁሉም ትምህርት ቤቶች በትምህርት አመቱ መገባደጃ ላይ ተማሪዎች ለሊተርሲ እና ለሂሳብ ትምህርት እንዲሁም ለደህንነት እና የተመቻቸ የትምህርት ቤት ድባብ ቅድሚያ ይሰጣሉ። ትምህርት ቤቶች ከት/ቤት የድጋፍ እና ደህንነት ዲሬክተር እና ከቡድኖቻቸው ጋር አብሮ በመሥራት የትምህርት ቤት ማሻሻያ እቅዶችን ለማዘጋጀት፣ ስራቸውን ለመከታተል እና እነዚህን ግቦች ለማሳካት ለሰራተኞች ድጋፍ እና ትምህርት ይሰጣሉ።

» ሥርዓት አቀፍ ሥልጠና መስጠት

MCPS በሊተርሲ እና በሂሳብ ትምህርት ለአስተማሪዎች፣ ለት/ቤት አመራሮች እና ለዋና ጽ/ቤት አመራሮች የሙያ ማዳበር ትምህርትን በተመለከተ ሦስት ቁልፍ መስኮችን ለይቷል። የአንደኛ ደረጃ ሊተርሲ ትምህርትን ለመደገፍ፣ የሙያ ማዳበር ትምህርት ትኩረት ያደረገው መሰረታዊ የሊትተርሲ መዋቅራዊ ለውጥ ላይ ነው። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ፣ ትኩረት የተደረገው በሁሉም የይዘት መስኮች የሊተርሲ ትምህርት ማዳበር ላይ ነው። በሂሳብ ትምህርት ይዘት ላይ በአንደኛ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚሰጠው የሙያ ማጎልበት ትምህርት የሂሳብ ትምህርትን በጥልቀት ለመረዳት ምርጥ ልምዶችን ይሠጣል። የትምህርት ስርዓቱ መምህራን፣ የት/ቤት መሪዎች እና የዋና ጽ/ቤት ሰራተኞች ሁሉም ይህንን ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል። በዚህ ሥራ ምክንያት፣ MCPS ከመዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል (K-12) ተማሪዎች የሊተርሲ እና የሂሳብ ትምህርት በክፍል ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ እንደሚሰሩ እንጠብቃለን፣ ስለዚህ ስርአተ ትምህርቱ እና የማስተማሩ ተግባር ከፍተኛ ጥራት ያለው እና በተማሪ የመማር ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ይሆናል።



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# ጣልቃ ገብነት/ Interventions



በክፍል ደረጃ ብቃታቸውን ያላሳዩ ተማሪዎች የጣልቃ ገብ ድጋፍ ይሰጣቸዋል።

በተግባር ላይ የዋሉ በማስረጃ የተረጋገጡ ጣልቃ ገብነቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

| የሊተርሲ ጣልቃ ገብነት | በክፍል ደረጃ ተግባራዊ ተደርጓል |
|---|---|
| Orton Gillingham (OG)፡- የንግግር ድምፅ፣ ስነልሣን፣ የምልክት መልክትን ወደ ቋንቋ መተርጎም እና መረጃን ወደ ምስጢራዊ ቋንቋ መቀየር ከፍተኛ ማሻሻል ለሚያስፈልጋቸው Tier III ተማሪዎች የንባብ ጣልቃ ገብነት ሊተገበሩ የሚችሉ ግልፅ፣ ስልታዊ እና ብዙ የስሜት ህዋሳት አጠቃቀም ዘዴዎችን ያስተምራል። | አንደኛ ደረጃ፣ መካከለኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |
| በጣም ጥሩ ንባብ (RGR) የድምፅ ግንዛቤ፣ የድምጽ ንግግር፣ ዲኮዲንግ እና ኢኮዲንግ ዘርፎች ጥልቅ ማሻሻል ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ግልጽ፣ ስልታዊ እና የተከማች Tier III የንባብ ጣልቃገብነት ይሰጣል። ለተማሪዎች ሦስት RGR ጣልቃ ገብነቶች ይኖራሉ፡- መቁጠር፣ ከፍ ያለ ድምፅ፣ እና HD ቃል | አንደኛ ደረጃ፣ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት |
| iReady Reading/ንባብ፡- የመረዳት ችሎታን ለማሻሻል ከፍተኛ ድጋፍ ለሚፈልጉ ተማሪዎች ግልፅ እና ስልታዊ Tier III ጣልቃ ገብነት ይሰጣል። | አንደኛ ደረጃ |
| System 44 መሠረታዊ የሊተርሲ ክህሎትን ያዳብራል | መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |
| ንባብ/Read 180፡ አጠቃላይ ግንዛቤ እና ትርጉም ያለው የንባብ ችሎታ ማዳበር ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች መሰረታዊ የንባብ ክህሎቶችን ይሰጣል። | መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |
| iLit: 4ኛ፣ 5ኛ ክፍል፣ በመካከለኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሚገኙ ESL ተማሪዎች ተጨማሪ የሊተርሲ ድጋፍ ይሰጣል | አንደኛ ደረጃ፣ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |
| **የሂሳብ ትምህርት ጣልቃ ገብነት** | **በክፍል ደረጃ ተሰጧል** |
| iReady Math/ሒሳብ የሂሳብ ትምህርት ማሻሻል ለሚፈልጉ ተማሪዎች ከፍተኛ ግልፅ እና ስልታዊ Tier III ጣልቃ ገብነት ይሰጣል። | አንደኛ ደረጃ ት/ቤት |
| ሒሳብ/Math 180፡- ለአልጀብራ 1 ለማዘጋጀት መሰረታዊ የሂሳብ ክህሎትን ይሰጣል | መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |

ለግምገማ እና ለትንተና የተሰበሰበው የጣልቃ ገብነት መረጃ የእያንዳንዱን ተማሪ የትምህርት ምዘና እቅድ በእያንዳንዱ ጣልቃ ገብነት መጨረሻ ላይ ለማሳወቅ ጥቅም ላይ ይውላል። የግምገማው ዕቅድ ለአስተማሪዎች እና ለወላጆች ይሰጣል። የልየታ መረጃ ከዕለታዊ የማሻሻል ሪፖርት ጋር በግምገማ እቅድ ውስጥ ይካተታል። በተጨማሪም፣ MCPS ተማሪዎችን ለመደገፍ የጸደቁትን የጣልቃ ገብነት መርሃ ግብሮች የሚያስከትሉትን ለውጦች እና ቅልጥፍናን ለመገምገም የጣልቃ ገብነት ውሂብ ከበርካታ መመዘኛዎች እና ተጨባጭ መረጃዎች ጋር ይተገበራል። በጣልቃ ገብ ጥረት ላይ መገኘትና መጠቀም ስኬትን ለመለካት ጥቅም ላይ ይውላል።

## የቅዳሜ ትምህርት ቤት/Saturday School

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች "George B. Thomas Learning Academy" በሚሰጥ የቅዳሜ ትምህርት ቤት ተጨማሪ የአካዳሚክ ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ።



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# ምን ይጠበቃል፦ ልዩ ትምህርት/Special Education



የልዩ ትምህርት ቢሮ የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ደንብ (IDEA)፣ በሜሪላንድ ህግጋት (COMAR) እና MSDE መመሪያ መሰረት የቅድመ ጣልቃ ገብነት እና የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን መተግበር ይቀጥላል።

ቅድመ ጣልቃ ገብነት እና የልዩ ትምህርት አገልግሎት ከልደት እስከ 21 አመት እድሜ ላላቸው ተማሪዎች ይሰጣሉ። በግለሰብ የመማር ሁኔታ ላይ ተመርኩዞ የሚሰጥ የትምህርት መርሃ ግብር (IEPs) ላላቸው ተማሪዎች በልዩ ሁኔታ የተነደፈ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች በተማሪው(ዋ) IEP በተመዘገበው መሰረት ይሰጣሉ። ዲስትሪክቱ በፌዴራል እና በስቴት ደንቦች መሠረት የልዩ ትምህርት ግዴታዎችን የማሟላት አሠራሮችን ያዘጋጃል። እነዚህ ግዴታዎች ከግምገማዎች ጋር የተያያዙ የጊዜ ሰሌዳዎችን እና ሰነዶችን፣ IEP ቡድን ስብሰባዎችን እና በልዩ ሁኔታ የተነደፉ መመሪያዎችን እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ያካትታሉ። ሁሉም ተማሪዎች IEP ወይም በግለሰብ የቤተሰብ አገልግሎት እቅድ (IFSP) ላይ በተገለፀው መሰረት ሙሉ አገልግሎት ያገኛሉ። ከመረጃዎች ግምገማ በኋላ በእነዚህ ሰነዶች ላይ ለውጦች አስፈላጊ ከሆኑ IEP ቡድኖች አገልግሎቶችን ለመተግበር እና/ወይም አስፈላጊ የሆኑትን IFSP/IEP ስብሰባዎች ለመጥራት ሁሉንም ህጋዊ ሂደቶች ይከተላሉ።

ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚያስፈልጉ የማስተማሪያ እና/ወይም አጋዥ ቴክኖሎጂዎች ይሰጣሉ። ለአጠቃላይ ትምህርት፣ ለልዩ ትምህርት እና ለእንግሊዘኛ ቋንቋ መዳበር (ELD) መምህራን፣ የአስተማሪ ረዳቶች፣ ተዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎች እና አስተዳዳሪዎች የሙያ ማዳበር ትምህርት እና በሥራቸው ላይ ያተኮረ የሥልጠና እድሎች ይሰጣሉ። እነዚህ እድሎች በልዩ ሁኔታ የተነደፉ መመሪያዎችን፣ Tier III በማስረጃ ላይ የተመሰረተ የማንበብ፣ የመጻፍ እና የሂሳብ ጣልቃገብነት፣ የባህሪ እና ማህበራዊ ስሜታዊ ድጋፎችን እና ስልቶችን፣ እና የማስተማሪያ/ቴክኖሎጂያዊ መርጃዎችን የሚመለከቱ ናቸው።

## ህፃናትና ትንንሽ ልጆች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የህፃናት እና ታዳጊዎች ፕሮግራም (MCITP) በቤት ውስጥ ወይም በሌላ የተፈጥሮ አካባቢ በአካል ተገኝቶ አገልግሎት ይሰጣል። ወላጆች/አሳዳጊዎች ፍላጎታቸውን ለማሟላት ቨርቹዋል አገልግሎቶች እንዲሰጣቸው መምረጥ ይችላሉ።

## ቻይልድ ፋይንድ (Child Find)

3-5 አመት እድሜ ያላቸው ተማሪዎች ምልመላ እና ግምገማ በአካል በመገኘት ይከናወናሉ። በልዩ ሁኔታዎች ቨርቹወል ማጣሪያ ሊከናወን ይችላል። የማጣራት እና የግምገማ እርምጃዎች ሰፊ የወላጅ/አሳዳጊ ቃለ መጠይቅ፣ የቅድመ ትምህርት ቤት መምህር ቃለመጠይቅ፣ መደበኛ ያልሆኑ የእድገት እንቅስቃሴዎች እና ሌሎች ዶኩመንቶችን መፈተሽ የመሣሰሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ። ደረጃቸውን የጠበቁ መለኪያዎች ማለት፥ የወላጅ/አሳዳጊ ደረጃ መለኪያዎችን ጭምር የሚከናወኑ በተግባር እና/ወይም በአካል በመገኘት የእያንዳንዱ ግምገማ መመዘኛዎች እና የተማሪው(ዋ) ግላዊ ፍላጎቶች ናቸው። በቤታቸው ወይም ህጻናት እንክብካቤ በሚደረግላቸው አካባቢ የተማሪው(ዋ) ቀጥተኛ ምልከታ የሚካሄደው ሲያስፈልግ እና ሲቻል ነው። የግምገማው ውጤት በመጀመሪያው IEP የብቃት ማጣራት ስብሰባ ላይ ለቤተሰቦች ይገለጻል። ልጁን/ልጅቱን ለመዋዕለ ሕፃናት ለማዘጋጀት የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን ማግኘት ተገቢ ከሆነ IEP ይዘጋጃል።

ከመዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል (K-12) እና/ወይም እስከ 21 ዓመት እድሜ ላሉ ተማሪዎች ማጣሪያ እና ግምገማዎች በአካል ይካሄዳሉ። የወላጅ/አሳዳጊ መመዘኛዎችን ጭምር ደረጃቸውን የጠበቁ እርምጃዎች፡



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# ልዩ ትምህርት (ቀጣይ)

በሙያ ቴራፒስቶች፣ በፊዚካል ቴራፒስቶች፣ በንግግር/ቋንቋ ፓቶሎጂስቶች እና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎች የሚደረጉ ግምገማዎች በአብዛኛው ሁኔታ በአካል ይካሄዳሉ። ግምገማዎች የወላጅ/አሳዳጊ ቃለመጠይቆችን፣ የተማሪ ምልከታዎችን እና እንደአግባቡ ደረጃቸውን የጠበቁ ሌሎች ተግባሮችን ሊያካትቱ ይችላሉ።

## አገልግሎት መስጠት

MCPS እምብዛም መሰናክል በሌለበት ሁኔታ ለተማሪዎች አገልግሎት መስጠት ይቀጥላል። የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እንዲማሩ እና የአካል ጉዳተኛ ካልሆኑ እኩዮቻቸው ጋር የትምህርት እድገት እንዲኖራቸው እና ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር እንዲሳተፉ ቀጣይነት ያለው አጽንኦት በመስጠት ለሁሉም ተማሪዎች የሚሰጠውን የትምህርት እድሎችን ልዩነት እንዲያጠቡ የትምህርት ቤት ቡድኖች ይበረታታሉ።

## የማካካሻ አገልግሎቶች

ከዚህ ቀደም የማካካስ/የማገገሚያ አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ ሆነው የተገኙ 2023 ሠመር መጨረሻ ላይ አገልግሎታቸው የማይጠናቀቅ ተማሪዎች ከዚህ በፊት የሚሰጣቸውን አገልግሎት 2023-2024 የትምህርት አመት ላይ ማግኘት ይቀጥላሉ።

## በድንገተኛ ሁኔታዎች IEP መተግበር

ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በልዩ ሁኔታ የተነደፈ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች በተማሪው(ዋ) IEP የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች እቅድ ላይ በተመዘገበው መሠረት ተግባራዊ ይሆናሉ። MCPS ለትምህርት ቤት ቡድኖች MSDE የቴክኒክ ድጋፍ መግለጫ/ቡሌቲን ሰጥቷል፡- ልዩ ትምህርት - ቀጣይ የትምህርት እቅድ - በድንገት ትምህርት ቤት በሚዘጋበት ወቅት የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን ቀጣይነት ማረጋገጥ አስፈላጊነት።

## የሰክሽን 504 እቅዶች (Section 504 Plans)

ሰክሽን 504 ዕቅዶች ያላቸው ሁሉም ተማሪዎች መረጃዎቻቸው ይመቻችላቸዋል። የሰክሽን 504 እቅድ ኬዝ ማናጀር እንደአስፈላጊነቱ ወይም በወላጅ/በአሳዳጊ ጥያቄ በየትምህርት ዓመቱ ቢያንስ አንድ ጊዜ ቨርቹዋል ወይም በአካል የሰክሽን 504 እቅድ ስብሰባዎችን ያስተባብራል።

የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎትን በሚመለከት ጥያቄዎች ካለዎት እባክዎን ከት/ቤት ርዕሰ መምህር እና/ወይም የልዩ ትምህርት አገልግሎት ቢሮ ጋር 240-740-3900 ደውለው ያነጋግሩ።

# ምን እንደሚጠበቅ፡- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ቨርቹወል አካደሚ (MCPS Virtual Academy)



2023-2024 የትምህርት ዓመት፣ MCPS ቨርቹወል ፕሮግራም ከአንደኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል ተማሪዎችን የሚያገለግል ይሆናል፥ የፀደቀውን MCPS የትምህርት ካላንደር በመከተል 180-ቀናት ጥምር የትምህርት ሞዴል ይጠቀማል። ጥምር የትምህርት ሞዴል የቀጥታ እና የተናጠል ሁለቱንም የትምህርት ሞዴል ያካትታል። ይህ ማለት ተማሪዎች በጥምር የትምህርት ተሞክሮዎች  ይሳተፋሉ-አንዳንድ የትምህርት ክፍል ጊዜዎች በአንድ ላይ ከመላው የክፍል ተማሪዎች ጋር በመምህራን የሚመራ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ የተናጠል ትምህርት ይሰጣል። MVA ተቀዳሚ ትኩረቱ፣ ሰራተኞች የተማሪዎቻቸውን ፍላጎቶች በሚያውቁበት እና ተማሪዎች በላቀ ሁኔታ ስኬታማ የሚሆኑበትን የትምህርት ቦታና ሁኔታ የሁሉንም ተማሪዎች ግላዊ ፍላጎቶች የሚያሟላ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አካታች የኦንላይን ትምህርትን ማበልፀግ ነው። ፕሮግራሙ የሚከተሉትን ዋና ዋና ነገሮች ያካትታል፡-

- የተለመደ/መደበኛ የአጠቃላይ ትምህርት ኮርሶችን መስጠት
- የተፋጠነ እና የላቀ ትምህርት ኮርሶች
- ክለቦች እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚካሄዱ ተጓዳኝ እንቅስቃሴዎች
- ተማሪዎች የተራዘመ የመማር እድል እና ልምዶችን የሚቀስሙበት ተሳትፎ፣ ድጋፍ፣ ጥራት ያለው የትምህርት ይዘት፣ እና ቀጥታ ማስተማር ይኖራል።

በተጨማሪም፣ እየሠሩ ለሚማሩ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ ከትምህርት ቤት ውጪ ያሉ አማራጮችን ለሚፈልጉ እና በአካባቢያቸው ትምህርት ቤት የማይገኙ የተፋጠነ እና የላቀ ኮርስ ለመማር ለሚፈልጉ MVA ልዩ እድል ይሰጣል።

ተማሪዎች COMAR ደንቦችን የሚያከብር እና በኦንላይን የተዘጋጀ መመሪያን የሚደግፍ ቤል (bell) መርሃ ግብር ይከተላሉ። የቀጥታ ትምህርቶች ስርጭት በየቀኑ ከሰኞ እስከ ዓርብ የሚካሄድ ሲሆን፣ ኮርሶቹ በአካል ከሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ክፍለጊዜዎች ጋር በቅርበት ይቀናጃሉ። የተለያዩ የትምህርት ደረጃዎችን ለማስተናገድ የመነሻ እና የማብቂያ ሠአቶችን በማስተካከል እንደ መደበኛ ትምህርት ቤት መርሃ ግብሮች ተመሳሳይ የትምህርት ሰዓት ይኖራቸዋል። ተማሪዎች ከትምህርት ክፍሎቻቸው መምህራን በትምህርታዊ ፍላጎቶቻቸው ላይ ተጨማሪ ጊዜ እና ድጋፍ ለመስጠት የድጋፍ እና የመግቢያ ጊዜዎችን ለማካተት ዕለታዊ መርሃ ግብሩ በየደረጃው ይስተካከላል። የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ሰዓቶች የተማሪ ሪኮርድ አካል ሆነው ይመዘገባሉ፥ እና የቨርቹዋል አካዳሚ ተማሪዎች ይህንን መስፈርት የሚያሟሉበትን እድሎች ያካተተ ይሆናል።

በአካላዊ ወይም በስሜታዊ ሁኔታዎች የተነሳ በተመደቡበት ት/ቤት ትምህርት መከታተል የማይችሉ በመሆኑ ዲጂታል (digital) የትምህርት እድል ለሚፈልጉ ተማሪዎች፣ MCPS የመሸጋገሪያ/ኢንተሪም ትምህርት አገልግሎቶችን ይሰጣል።

በተጨማሪም MCPS ለመመሪቂያ ፕሮግራሞች የኦንላይን ትምህርቶችን አዘጋጅቷል፣ ይሄም መሟላት ያለበትን የመመረቂያ ኮርስ/ትምህርት ማግኘት ለሚፈልጉ ተማሪዎች ነው።

በእነዚህ ፕሮግራሞች ላይ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ እባክዎን ይሄንን ይጎብኙ፡-

- Interim Instructional Services
  የሽግግር/ኢንተሪም የማስተማር አገልግሎቶች
- ኦንላይን የሚሰጡ ትምህርቶች/Online Pathways

# ውጤት አሰጣጥ፣ በትምህርት መገኘት፣ ተሳትፎ እና ኃላፊነት-ተጠያቂነት



## ስለ ማርክ አሠጣጥ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) 2023–2024 የትምህርት ዓመት "MCPS Regulation IKA-RA" የውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት አቀራረብ እንደተዘረዘረው ወደ ቅድመ-ወረርሽኝ የውጤት/የማርክ  አሰጣጥ ፖሊሲዎችና ሂደቶች ይመለሳል።

ምርጥ ተሞክሮዎች የሚያካትቱት:-

- ተማሪዎችን ማስቀደም እና ተገቢነት ያለው የውጤት አሰጣጥ። ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች እንደገና ግምገማ ማድረግ እና እንደሁኔታው የማመቻቸት በርካታ እድሎችን ይሰጧቸዋል። MCPS ተማሪዎች በወረርሽኙ ወቅት ያጋጠሟቸውን እጅግ በጣም ከባድ ፈተናዎች ያስታውሳል፥ እናም በማገገሚያ ወቅትም ይኼው ተግዳሮት ይቀጥላል።
- በእያንዳንዱ የማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ የሚመከሩ የተለያዩ በርካታ ስራዎችን መሥራት።
- በሁሉም ኮርሶች ወጥ የሆነ የውጤት ምዝገባዎችን (90% በሁሉም ምዘናዎች፣ ለልምምድ እና ዝግጅት 10% መተግበሩን) ማረጋገጥ።
- የ "50% ደንብ" ቀጣይ አጠቃቀም እና የሁለትዮሽ ግንኙነት ላይ አጽእኖት ይሰጣል።
- ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች (ESOL) የእንግሊዝኛ እና የሒሳብ ኮርሶች ለዲስትሪክት ምዘናዎች የሚፈለገውን 10% ውጤት በማስወገድ ውጤቱን በሌላ የትምህርት ምድብ እንዲሟላ ይደረጋል።

በተጨማሪም MCPS ከክሬዲት ማገገሚያ፣ ትምህርት የመከታተል ጣልቃ ገብነት እና የውጤት ማሻሻያ ትግበራን በሚመለከት ወደ ቅድመ ወረርሽኙ ወቅት ይመለሳል።

## ኃላፊነት-ተጠያቂነት

### MCPS የመማር ማረጋገጫ ማዕቀፍ

የተማሪ ውጤት ሲገመግም፣ MCPS የሚከተሉትን ጥያቄዎች የሚመልስ መሆን አለበት:-

- ልጆች እየተማሩ ናቸው?
- በቂ ትምህርት/ዕውቀት እየቀሰሙ ናቸው?
- እንዴት እናውቃለን?
- ካልሆነስ፣ ለምን አልሆነም?
- ስለዚህ ምን ማድረግ ይኖርብናል?

የተማሪን ግስጋሴ ሙሉ ሥዕል ለማግኘት፣ ዲስትሪክቱ ተማሪዎች እንዴት እየሰሩ እንደሆነ ለመገምገም በርካታ መለኪያዎችን/መመዘኛዎችን ይጠቀማል። እነዚህ እርምጃዎች የተማሪን የትምህርት እድገት በሚገመግሙ  የክፍል፣ የዲስትሪክት እና ውጫዊ አውዶች የሚከናወኑ ናቸው።

| | |
|---|---|
| የመማሪያ ክፍል ዳታ/መረጃ | ሪፖርት ካርድ |
| የዲስትሪክት ፈተና/ምዘና | የዲስትሪክቱ ግምገማዎች በቀጥታ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከሥርዓት ትምህርት ደረጃዎች ጋር የተጣጣሙ ናቸው |
| ውጫዊ ምዘና | የስቴት/ናሽናል ምዘናዎች |

# ውጤት፣ በትምህርት ላይ መገኘት፣ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት (ቀጣይ)



## የመነሻ ልክ እና የተማሪ ውጤት ማመሣከሪያ

2020-2021 የትምህርት ማስረጃ ማዕቀፍ ተማሪዎች በሊተርሲ እና በሂሳብ ትምህርት ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ለማወቅ እንደ መነሻ መረጃች ሆኖ ያገለግላል። ይህ ማዕቀፍ የተለያዩ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነ ጥበብ እና የሂሳብ መመዘኛ እያንዳንዳቸው ከሶስት ምድቦች በአንዱ የተመደቡ ናቸው፡ ክፍል፣ ዲስትሪክት፣ ወይም ውጫዊ። ከዚህ በታች የሚገኙት ለመጀመሪያ፣ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የመነሻ መረጃ ዝርዝር ሰንጠረዦች ከተማሪ ውጤት ጋር በዘር፣ በአገልግሎት ቡድን እና በፆታ ተከፋፍለው ነው።

## አንደኛ ደረጃ/ኤለመንተሪ ት/ቤት

| | EOL ሊተርሲ ከመቶኛ | ለ 2025 የትምህርት ዘመን 90% ግብ የታለመ | የተጠናቀቀ EOL ሂሳብ በመቶኛ/ፐርሰንት | ለ 2025 ግብ 90% የታለመ |
|---|---|---|---|---|
| ሴት | 59.2 | 66.9 | 59.0 | 66.8 |
| ወንድ | 53.4 | 62.6 | 59.5 | 67.1 |
| ኤዥያዊ | 77.6 | 80.7 | 83.4 | 85.1 |
| ጥቁር ወይም አፍሪካን አሜሪካን | 51.1 | 60.8 | 50.2 | 60.2 |
| ሂስፓኒክ/ላቲኖ | 33.4 | 47.6 | 37.0 | 50.3 |
| ነጭ | 76.4 | 79.8 | 80.8 | 83.1 |
| ከሁሉም ሌላ | 70.2 | 75.2 | 72.5 | 76.9 |
| የነጻ እና የቅናሽ ዋጋ ምግብ ስርዓት | 32.9 | 47.2 | 35.3 | 49.0 |
| ልዩ ትምህርት/ስፔሻል ኢጁኬሽን | 30.8 | 45.6 | 36.0 | 49.5 |
| ውስን የእንግሊዘኛ ችሎታ | 31.1 | 45.8 | 36.8 | 50.1 |



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# ውጤት፣ በትምህርት ላይ መገኘት፣ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት (ቀጣይ)



## መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት

| | EOL ሊ.ተርሲ ከመቶኛ | ለ 2025 ግብ 90% የታለመ | የተጠናቀቀ EOL ሂሳብ በመቶኛ/ ፐርሰንት | ለ 2025 ግብ 90% የታለመ |
|---|---|---|---|---|
| ሴት | 73.6 | 77.7 | 60.0 | 67.5 |
| ወንድ | 66.5 | 72.4 | 55.8 | 64.4 |
| ኤዥያዊ | 87.4 | 88.1 | 84.8 | 86.1 |
| ጥቁር ወይም አፍሪካን አሜሪካን | 63.9 | 70.4 | 45.6 | 56.7 |
| ሂስፓኒክ/ላቲኖ | 50.5 | 60.4 | 34.5 | 48.4 |
| ነጭ | 88.0 | 88.5 | 80.0 | 82.5 |
| ሌላ ሁሉም | 79.1 | 81.8 | 70.3 | 75.2 |
| የነጻ እና የቅናሽ ዋጋ ምግብ ስርዓት | 48.8 | 59.1 | 32.7 | 47.0 |
| ልዩ ትምህርት | 53.3 | 62.5 | 31.4 | 46.1 |
| ውስን የእንግሊዘኛ ችሎታ | 45.5 | 56.6 | 26.1 | 42.1 |



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# ውጤት፤ ትምህርት ላይ መገኘት፤ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት (ቀጣይ)



## ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

| | EOL ሊተርሲ ከመቶኛ | ለ 2025 ግብ 90% የታለመ | የተጠናቀቀ EOL ሂሳብ በመቶኛ/ፐርሰንት | ለ 2025 ግብ 90% የታለመ |
|---|---|---|---|---|
| ሴት | 78.5 | 81.4 | 73.8 | 77.9 |
| ወንድ | 70.3 | 75.2 | 65.3 | 71.5 |
| ኤዥያዊ | 89.8 | 89.9 | 88.7 | 89.0 |
| ጥቁር ወይም አፍሪካን አሜሪካን | 69.6 | 74.7 | 62.2 | 69.2 |
| ሂስፓኒክ/ላቲኖ | 54.7 | 63.5 | 48.9 | 59.2 |
| ነጭ | 90.0 | 90.0 | 86.3 | 87.2 |
| ሌላ ሁሉም | 83.0 | 84.8 | 76.7 | 80.0 |
| የነጻ እና የቅናሽ ዋጋ ምግብ ስርዓት | 55.1 | 63.8 | 48.8 | 59.1 |
| ልዩ ትምህርት | 57.8 | 65.9 | 47.0 | 57.8 |
| ውስን የእንግሊዘኛ ችሎታ | 38.3 | 51.2 | 36.2 | 49.7 |

ተማሪዎች ማወቅ ያለባቸውን ትምህርቶች ተፅዕኖ ለመገመት፣ የተለያዩ የመረጃ አያያዞች በተማሪ ቡድኖች፣ የመማሪያ ክፍሎች መረጃ (ማለትም ውጤቶቻቸውን)፣ በዲስትሪክት ደረጃ ከትምህርት ስርዓቱ ጋር የሚጣጣሙ ምዘናዎች እና መደበኛ ግምገማዎች ይደረጋሉ።

የአፈጻጸም ልዩነቶችን ለማወቅ የውጤት መረጃዎቹ ከክፍል ደረጃ እኩዮች ውጤት እና ከብሔራዊ የውጤት መረጃዎች ጋር ይነጻፀራል። በንባብ እና በሂሳብ ትምህርት የአካዳሚክ እድገት መለኪያዎች (MAP) ያገኙት ውጤት ይነጻጸራል።

# ኃላፊነት-ተጠያቂነት (የቀጠለ)



## MCPS የትምህርት ማዕቀፍ ማስረጃ (ቀጣይ)

የመማር ማዕቀፍ ማረጋገጫ የተማሪን ትምህርት ለመገምገም የሚያገለግሉ የተለያዩ የመማሪያ ክፍል፣ የዲስትሪክት እና የውጭ አካል የሚሰጣቸውን ምዘናዎች ያጠቃልላል። ማዕቀፉ የተማሪን ዝግጁነት እና ስኬት ተጠያቂነትን የሚለይ የብዙ መመዘኛ እርምጃዎችን አቀራረብ ይጠቀማል። የማዕቀፉ ዓላማ ተማሪ እየተማረ(ች) እንደሆነ ወይም ትምህርቱ ምን ያህል እንደገባቸው ማሳየት እንደሚችሉ የማወቅ መለኪያ ነው። የብዙ መመዘኛዎች አቀራረብ ተማሪዎች የተማሩትን እውቀት ለማሳየት እድሎችን ይጨምራል እናም ተማሪዎች የሚያውቁትን እና ማድረግ የሚችሉትን የበለጠ የተሟላ ምስል ይሰጣል። የመማር ውጤት መሻሻል ለማያሳዩ ተማሪዎች ትምህርት እና ስኬታቸውን ለማሳደግ የማስተማር ጣልቃ ገብነት የመሣሰሉ ድጋፎች ይሰጣሉ።

ተጨማሪ ድጋፎች የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ለመለየት ጥቅም ላይ የሚውለው የመማር ማዕቀፍ ማስረጃ አንዱ ገጽታ NWEA የአካዳሚክ እድገት እርምጃዎች (MAP) የትምህርት እድገት ውጫዊ መመዘኛ ነው። NWEA MAP የአካደሚክ እድገት ምዘናዎች ከክፍል-ደረጃ እኩዮቻቸው ጋር ብቻ ሳይሆን ከብሔራዊ የትምህርት እኩዮቻቸው ጋር ማነጻፀርንም ይጨምራል። ስለ MAP እድገት ፎል ላይ ውጫዊ ምዘና ለማካሄድ፣ የሚከተሉት መለኪያዎች ከአንደኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላሉ ተማሪዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ።

### ሰፕቴምበር/ኦክቶበር 2021 ላይ የተሰጠ የውጭ ግምገማ

| ደረጃ | ሊተርሲ | ሂሳብ | የመለካት ዘዴ |
|---|---|---|---|
| አንደኛ ደረጃ (ኤሌሜንተሪ) ት/ቤት፡- ከመዋእለ ህጻናት እስከ 2ኛ ክፍል | MAP የማንበብ ቅልጥፍና | MAP-የመጀመሪያ ደረጃ | ከናሽናል 50 ፐርሰንት ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ አፈፃፀም |
| አንደኛ ደረጃ/ኤሌሜንታሪ ት/ቤት፡- 3ኛ እስከ 5ኛ ክፍል | MAP እድገት - ንባብ | MAP እድገት – ሒሳብ | በናሽናል 50 ፐርሰንት ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ አፈፃፀም |
| መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (Middle School) | MAP እድገት - ንባብ | MAP እድገት - ሒሳብ | በናሽናል 50 ፐርሰንት ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ አፈፃፀም |
| ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (High School) | MAP እድገት - ንባብ | MAP እድገት - ሒሳብ | በናሽናል 50 ፐርሰንት ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ አፈፃፀም |

* አፈፃፀም የሚለካው NWEA በደነገገው መሠረት የክፍል-ደረጃ መስፈርቱን ለሚያሟሉ ወይም ከዚያ በላይ ውጤት ለሚያመጡ ተማሪዎች ነው።

# ትምህርት መከታተል

## ትምህርት መከታተልን ሪፖርት ስለማድረግ

በትምህርት ቤት ስለመገኘት ፖሊሲ "MCPS Regulation JEA-RA" የተማሪ ትምህርት መከታተል በሚለው ላይ ተገልጿል። ይህም የእለት ተእለት ትምህርት ላይ መገኘትን፣ መዘግየትን፣ በፈቃድ መቅረትን እና ያለምክንያት መቅረትን፣ ሪኮርድ እና ሪፖርት ማድረግን ይጨምራል። ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ በእያንዳንዱ የትምህርት ቀን መጀመሪያ ላይ ተማሪዎች መገኘታቸው በየቀኑ ይመዘገባል። 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣የተማሪዎች በትምህርት ላይ መገኘት በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ እየተመዘገበ የእለት ተእለት የመገኘት ኮድ ጋር ይሰላል።

የተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት በአስተማሪዎች ቁጥጥር እየተደረገ Synergy የተማሪ መረጃ ቋት ውስጥ ይመዘገባል። ይህ መረጃ በወላጅ "ParentVUE" ፖርታል በኩል ለወላጆች ይተላለፋል። ተማሪ እንደሌለ(ች) ምልክት ሲደረግ፣ በአውቶሜትድ ጥሪ ተማሪው(ዋ) እንደሌለ(ች) ለወላጅ/አሳዳጊ ይደርሳል። ይህ በፍጥነት ጣልቃ ለመግባት እና አስፈላጊ ከሆነ በትኩረት ክትትል ለማድረግ ይጠቅማል። የእለት ተእለት በትምህርት ላይ የመገኘት ሪፖርት በአከባቢ ት/ቤት ደረጃ ይወሰዳል፥ ይህም የት/ቤት መሪዎች የተማሪዎችን በትምህርት ላይ የመገኘት ሁኔታ ለመገምገም እና በመደበኛነት ትምህርት ቤት ለመከታተል ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ለመለየት ጠቃሚ ይሆናል። በመጀመሪያዎቹ ሶስት ሳምንታት የትምህርት ቤቶች ዋና ፅህፈት ቤት ሰራተኞች ወደ ትምህርት ቤት ያልተመለሱ ተማሪዎችን ለመለየት እና ለቤተሰቦች የማድረስ ሂደቶችን ለማቀድ በየቀኑ ይከታተላሉ። በት/ቤት እና በዲስትሪክት ደረጃ ያሉ በርካታ በተማሪዎች-ደረጃ በትምህርት ላይ የመገኘትን አጠቃላይ ሪፖርት ለመከታተል እና እንደ አስፈላጊነቱ ፈጣን የጣልቃገብነት እርምጃ ለመውሰድ ያገለግላሉ።

ትምህርት ላይ የመገኘት ክትትል እና ጣልቃገብነት ኦፐሬሽን መመሪያበተማሪ እና በቤተሰብ ድጋፍ እና ተሳትፎ እና በልዩ ትምህርት ቢሮ የተቀናጀ አሠራር ለተማሪዎቻችን የታለመውን ያልተቋረጠ የመገኘት እና የተሳትፎ ሁኔታዎች ጣልቃገብነቶችን ተግባራዊ ስለማድረግ ማብራሪያ ይሰጣል።

## የደህንነት-ቁመና ቡድኖች

2022-2023 የትምህርት አመት፣ ት/ቤት መከታተል እና መሳተፍ የሚቸገሩ ተማሪዎችን፣ ማህበራዊ-ስሜታዊ ችግሮች ያጋጠማቸው ተማሪዎችን፣ እና የት/ቤት ስርዓት እና የማህበረሰብ መገልገያ ሪሶርሶች/ግብዓቶችን ለሚፈልጉ ቤተሰቦች ተደራሽ ለማድረግ ሁሉም ት/ቤቶች የተማሪዎች የደህንነት-ቁመና ቡድኖቻቸውን በመለወጥ አሻሽለዋል። የተማሪዎች ደህንነት-ቁመና ቡድኖች ቁልፍ አባላት የት/ቤት አስተዳደሮች፣ የት/ቤት ካውንስለሮች፣ የተማሪ ተወካይ ሰራተኞች (PPWs)፣ ማህበራዊ ሰራተኞች፣ የት/ቤት ስነ-ልቦና ባለሙያዎች፣ የወላጅ ማህበረሰብ አስተባባሪዎች (PCCs)፣ እና የብዝሃ-ቋንቋ ተናጋሪ ቴራፒቲክ ካውንስለሮች (ETCs) ናቸው። የተማሪ ደህንነት-ቁመና ቡድኖች መረጃዎችን ይተነትናሉ፣ የመነሻ ምክንያት ትንተናዎችን ያደርጋሉ፣ ከዚያ በመቀጠል ኢላማ የተደረጉ ማስተካከያዎችን ይተገብራሉ።

MCPS ባለብዙ-እርከን የድጋፍ ሲስተሞችን (MTSS) በማቀናጀት አዘጋጅቷል። MTSS መድረክ ለተማሪዎች የማስተካከያ ጣልቃ-ገብነቶች በማህበራዊ-ስሜታዊ ድጋፍ፣ በባህሪ ቅኝት ድጋፍ፣ እና ትምህርት ላይ መገኘትን በሚመለከት መተግበራቸውን ት/ቤቶች፣ እና ዲስትሪክቱ መቆጣጠር እና መመዘን እንዲችሉ ያደርጋል። የተማሪዎች የደህንነት-ቁመና ቡድን አባላት በሁሉም 210 ት/ቤቶች ውስጥ ስለ MTSS መድረክ 2022 ፎል ላይ ስልጠና ወስደዋል። 2022-2023 የትምህርት ዘመን በሁለተኛው ሴሚስተር በመድረኩ ዝቅተኛ የመልቀቅ ሁኔታ ታይቷል። የሠመር ሙያዊ ትምህርት 2023-2024 የትምህርት አመት መጀመሪያ ሙሉ MTSS መድረክ ከመጀመሩ በፊት ተካሂዷል። በዲስትሪክቱ ውስጥ ያሉ የተማሪ ደህንነት ቁመና ቡድኖች ወጥነት ባለው መልኩ መተግበሩን ለማረጋገጥ የኦፕሬሽን ማንዋል ለትምህርት ቤቶች ተሰራጭቷል።

## ቨርቹወል አካደሚ መከታተል/Virtual Academy Attendance

በቨርቹዋል አካዳሚ ላሉ ተማሪዎች በየእለቱ ተመሣሣይ ትምህርት ይሰጣል። ተማሪዎች በየቀኑ በክፍል መገኘት ይጠበቅባቸዋል። በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ፖሊሲ መሰረት፤ በአካል ከሚሰጠው ትምህርት መመሪያ ጋር በተጣጣመ መልኩ ክፍል ውስጥ መገኘት በየቀኑ ይመዘገባል። የመጀመሪያ ደረጃ አስተማሪዎች በጠዋት አንድ ጊዜ ይመዘግባሉ፣የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን በእያንዳንዱ የትምህርት ክፍለጊዜ መጀመሪያ ላይ ክፍል ውስጥ የተገኙትን/ያልተገኙትን እየተቆጣጠሩ ይመዘግባሉ። የሁለተኛ ደረጃ ክፍለ ጊዜ መገኘት በተማሪ የመረጃ ቋት ውስጥ በሲነርጂ/Synergy የተመዘገበውን የእለት ተእለት የክትትል ምዝገባ ለማስላት በአንድ ላይ ይከማቻል። ቨርቹዋል አካዳሚ በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት እና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሁለት የደህንነት/well-being ቡድኖች አሉት። እነዚህ ቡድኖች በየሳምንቱ እየተሰበሰቡ የሁሉንም ተማሪዎች የመገኘት እና የተሳትፎ መረጃ ይመረምራሉ። ተጨማሪ ትምህርት የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችን በመለየት ተማሪዎችን የመደገፍ አሠራሮችን እና እቅዶችን ያዘጋጃሉ። ሁሉም PPW በቨርቹዋል አካዳሚ ውስጥ ያሉትን ተማሪዎች ይደግፋሉ። ተማሪዎች አሁንም በአካባቢያቸው ትምህርት ቤት የተመዘገቡ በመሆናቸው፣ በቨርቹወል አካዳሚ ውስጥ ያሉ ካውንስለሮች በአካባቢ ትምህርት ቤት ከሚገኙ የካውንስል አገልግሎት አባላት ጋር የተቀናጀ ድጋፍ እና አገልግሎቶችን ይሰጣሉ።



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# የተማሪዎች፣ የሠራተኞች እና የቤተሰብ ድጋፎች



ወረርሽኙ የተማሪዎችን፣ የሰራተኞችን እና የቤተሰቦችን የትምህርት፣ የማህበራዊ፣ እና ስሜታዊ ጤናማነትን እንዴት እንደጎዳ MCPS ይገነዘባል። MCPS ተማሪዎች በአካል በመማር ከሚቀዳጁት አወንታዊ ማህበራዊ እና ስሜታዊ ተሞክሮዎች ጋር ማገናኘቱን ይቀጥላል።

MCPS ተማሪዎችን፣ ቤተሰቦችን እና ወላጆችን በማህበረሰብ ተደራሽነት እሳቤ በማሳተፍ፣ ዙርያውን የማህበረሰብ መገልገያ ቦታዎችን በመጎብኘት መረጃዎችን፣ ሪሶርሶችን እና የታለመ ድጋፍ ለቤተሰቦች ማድረስ ይቀጥላል። እንዲሁም ተማሪዎች፣ ወላጆች እና ቤተሰቦች ከትምህርት፣ ከማህበራዊ እና የጤና አገልግሎት ሪሶርሶች ጋር የሚገናኙበትን መንገዶች ለማመቻቸት MCPS ከካውንቲ ኤጀንሲዎች ጋር በአጋርነት ይሠራል። MCPS ለእያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 1.0 ማህበራዊ ሰራተኛ ቀጥሯል፤ ስራ አስጀምሯል። እነዚህ ማህበራዊ ሰራተኞች የተማሪ ደህንነት ቡድን ቁልፍ አካል ሆነው ያገለግላሉ። (የግንኙነት ዕቅዱን እዚህ ይመልከቱ)።

## ተማሪዎች

MCPS የተማሪዎችን፣ የቤተሰቦችን እና የሰራተኞችን አካላዊ፣ ማህበራዊ እና ስነ-ልቦናዊ ፍላጎቶች በዲስትሪክት እና በት/ቤት ባሉት ፕሮግራሞች የማሟላት ጥረቱን ይቀጥላል። "Be Well 365" የማገገሚያ እቅድ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የማህበረሰቡን እና የሰራተኞችን ስጋቶች ለመፍታት ትምህርት ቤቶች መውሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ይዘረዝራል። የማህበራዊ-ስሜታዊ (SEL) ትምህርቶች ከመዋዕለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ በተናጥል እና በተቀናጀ መልኩ ይከናወናሉ።

## ሠራተኞች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) 24,000 ለሚመልጡ ሰራተኞቹ አካላዊ፣ ማህበራዊ እና ስነ-ልቦናዊ ጤንነት በቁርጠኝነት ይሰራል። በሰራተኞች እና ጡረተኞች አገልግሎት ማእከል (ERSC) ያለው MCPS የሰራተኞች ደህንነት ፕሮግራም ለሰራተኞች ብዙ የጤና ትምህርት እድሎችን እና ፕሮግራሞችን የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ የጤና ጥቅማ ጥቅሞችን በማሰስ ጭምር ይደግፋል። የሰራተኞች እርዳታ ፕሮግራም ሰራተኞቹን እና አገልግሎቶችን፣ ግብዓቶችን እንዲሁም ድጋፍን በመጨመር ለሰራተኞቻቸው እና ለቤተሰቦቻቸው በካውንስሊንግ ክፍለ ጊዜዎች፣ የምክክር አገልግሎት፣ የቪዲዮ መልዕክቶች፣ ጋዜጣዎች፣ እና ጤነኛ ቁመና አውደ ጥናቶች የመሳሰሉትን ደህንነትን ስለመጠበቅ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ አገልግሎት መስጠቱን በስፋት ይቀጥላል። በተጨማሪም፣ ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች ከተጨማሪ ግብአቶች እና የጤንነት አጠባበቅ ዝግጅቶች ጋር ለተማሪዎች እና ለሰራተኞች ደህንነት ቅድሚያ መስጠታቸውን ይቀጥላሉ።

## ወላጆች እና ቤተሰቦች

MCPS ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸው ስኬታማ እንዲሆኑላቸው ለመርዳት የሚያስፈልጋቸውን ግብዓቶች፣ መሳሪያዎች እና መረጃዎችን መስጠቱን ይቀጥላል። የድጋፍ ሰራተኞች ምግብን፣ መኖሪያን፣ የአካል እና የአዕምሮ ጤናን ጨምሮ ከትምህርት ሲስተም እና ከማህበረሰብ ሪሶርሶች ጋር በማገናኘት ቤተሰቦችን ለመርዳት ዝግጁ ናቸው። ቤተሰቦች ለበለጠ መረጃ የት/ቤት ካውንስለር፣ የትምህርት ቤት ሳይኮሎጂስት፣ PPW፣ ESOL የሽግግር አማካሪ (ETC) ወይም PCC በትምህርት ቤታቸው ማነጋገር ይችላሉ። ወላጆች ስለ ማህበራዊ-ስሜት ጤነኛ ቁመና፣ ስለ ርቀት ትምህርት ስትራቴጂዎች እና ድጋፎች፣ የወላጅና ልጅ መልካም ግንኙነት፣ ስለ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና ሌሎችም በርካታ አርዕስቶች ላይ የተዘጋጁ ስልጠናዎችን፣ አውደ ጥናቶችን እና የተቀዱ የቪድዮ ከፍለጊዜዎችን ማግኘት ይችላሉ።

| የወላጆች አካደሚ/ PARENT ACADEMY | ስለ አእምሮ ጤንነት WAYMAKING | የጥንቃቄ-ወቅቶች |
| --- | --- | --- |
| www.montgomeryschoolsmd.org/departments/parentacademy/ | https://youtube.com/playlist?list=PLkZwAghwrSyvIgVRCWXjpiI4iBWRK0Lwl | www.youtube.com/playlist?list=PLkZwAghwrSytgi1re_2Sr8Dt8poZCHgP5 |




Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# የማህበረሰብ ተሳትፎ እና ግንኙነት



## የዲስትሪክቱ ስልታዊ ትግበራ ተነሳሽነት ቡድን

እንደገና ስለመክፈት እና የማገገሚያ ሂደት MCPS ኃላፊነት ባላቸው ቢሮዎች የተመቻቸ ትርጉም ያለው እና ቀጣይ የሆነ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ አግኝቷል። ባለድርሻ አካላት የወላጅ እና የማህበረሰብ ድርጅቶችን፣ የሰራተኛ ማህበራት እና የትምህርት ቤት እና የመስሪያ ቤት ሰራተኞችን ያካትታሉ። 2023 መልሶ የመክፈት እቅድ ስራ ላይ ግብአት የሰጡ ባለድርሻ አካላት የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

» የስርአተ ትምህርት አማካሪ ጉባኤ እና የትምህርት ዘርፍ ኮሚቴዎች

» የተፋጠነ እና የበለጸገ የማስተማር ግብረመልስ ካውንስል

» ትምህርት ላይ የመገኘት ሥራ ቡድን

» የልዩ ትምህርት ዜጎች አማካሪ ኮሚቴ

» የኮቪድ-19 ኦፐሬሽንስ አማካሪ ቡድን

MCPS የኮሚዩኒኬሽን ጽ/ቤት የግንኙነት እና የስርጭት ውጤታማነትን የማዳበር፣ የማስተዳደር እና የመከታተል ሃላፊነት አለበት። ለዚህ ቢሮ ኃላፊነት ያለው አካል የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ክሪስቶፈር ክራም (Christopher Cram) ነው።

ቢሮውን በሚከተሉት መንገዶች ማግኘት ይቻላል፡-

የዳይሬክተሩ ኢሜል: christopher_c_cram@mcpsmd.org
የጽ/ቤት ኢሜል: pio@mcpsmd.org or AskMCPS@mcpsmd.org
የቢሮ ስልክ፡ 240-740-2837
AskMCPS phone 240-740-3000 | Spanish Hotline: 240-740-2845



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# ቴክኖሎጂ

ትምህርት ቤቶች ለቴክኖሎጂ ተማሪ የተናጠል ሞዴል ወይም ካርት ሞዴል ተግባራዊ ለማድረግ ምርጫ አላቸው። አብዛኛዎቹ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶቻችን ተማሪዎች ክሮምቡክ (Chromebook) እና መያዣ ጋር የተመደቡበትን የተናጠል ሞዴል አግኝተዋል። በየቀኑ ከትምህርት ቤት ወደ ቤት ይዘውት እንዲመጡ ይጠበቃል። ይህ መገልገያ የማስተማር ስራዎችን ለማጠናቀቅ በትምህርት ቤት እና በቤት ውስጥ ጥቅም ላይ ይውላል።

የካርት ሞዴል የክሮምቡክስ (Chromebooks) ስብስቦች በትምህርት ቀን ጥቅም ላይ እንዲውሉ በእያንዳንዱ የትምህርት ክፍል ውስጥ ይቀመጣሉ። አብዛኛዎቹ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶቻችን ይህንን ሞዴል አግኝተዋል። በቤት ውስጥ ክሮምቡክ (Chromebook) ማግኘት የሚያስፈልጋቸው በእነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች አንዱን አስመዝግበው ያለምንም ወጪ  በትምህርት አመቱ ለአገልግሎት ቤታቸው መተው ይችላሉ።

## በአካል

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለመጪው የትምህርት ዓመት ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ በአካል ትምህርት እንደሚሰጥ ይጠበቃል። አስቸጋሪ ሁኔታ ያላቸው ተማሪዎች ለሞንትጎመሪ ቨርቹዋል አካዳሚ ማመልከት እና መከታተል አማራጭ ሲሆን እንዲሁም ለጊዜያዊ የማስተማሪያ አገልግሎት ማመልከት ይችላሉ። ሁሉም ተማሪዎች ለመማር ክሮምቡክስ (Chromebooks) እንደ ዋና መሳሪያቸው ይጠቀማሉ። MCPS Google አካውንት ለሁሉም ሰራተኞች እና ተማሪዎች ተሰጥቷል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከኦንላይን ማመልከቻዎች እና ስርአተ ትምህርት በተጨማሪ፣ የኮርስ ቁሳቁሶችን፣ የቤት ስራዎችን፣ የውይይት መድረኮችን፣ ጥያቄዎችን እና ሌሎችንም የሚያካትቱ የኦንላይን የኮርስ መስጫ ቋት ለመፍጠር ለመምህራን የካንቫስ ትምህርት አሰጣጥ ማኔጅመንት ሲስተም ይጠቀማል። የማስተማር ሒደት እና ምዘና እንከን የለሽ መሆን ስላለባቸው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)

## ቨርቹወል

የመገናኛ አውታረመረብ ሁሉንም የተማሪ እና የሰራተኞች የትምህርት መሳሪያዎችን መደገፍ ይችላል።

ወደ ቨርቹወል ማስተማር መቀየር አስፈላጊ ከሆነ፣ ሁሉም ተማሪዎች በቤት ውስጥ የሚጠቀሙበት ክሮምቡክ (Chromebook) ያገኛሉ። ወደ ቨርቹዋል ማስተማር የተመቻቸ ሽግግርን ለማድረግ "Nearpod" እና "Zoom" ኦንላይን የደንበኝነት ምዝገባዎችን ጭምር ተመሳሳይ የቴክኖሎጂ ግብዓቶች ጥቅም ላይ ይውላሉ። ካንቫስ እንደ ዋና የኮርስ መስጫ ቋት ጥቅም ላይ ይውላል።

## ካንቫስ

በአካል በማስተማር ወቅት፣ የካንቫስ መድረክን ለማስታወሻ፣ የሚቀርቡ ትምህርቶችን፣ ቪዲዮዎችን፣ የቤት ሥራዎችን፣ የቀን መቁጠሪያዎችን፣ ጥያቄዎች እና ሌሎችንም ጭምር የኮርስ ቁሳቁሶችን ለመጫን አስተማሪዎች ሊጠቀሙበት ይችላሉ። መምህራን ከፍተኛ ጥራት ያለው የማስተማር ስራዎችን ለማዘጋጀት ብዙ የኦንላይን እና ቁሳዊ ሪሶርሶችን መጠቀም ስለሚችሉ እነዚህ ኮርሶች ሁሉንም የክፍል ስራዎችን ሊያካትቱ ወይም ላያካትቱ ይችላሉ። የካንቫስ መድረክ ከኮርስ ማህደር ወይም ማሰሪያ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን መምህራን እና ተማሪዎች የሚያገኙት አንዱ የማስተማሪያ/የመማሪያ አገልግሎት መስጫ ነው።

የአጭር ጊዜ መቅረት ጉዳዮች ሲፈጠሩ የካንቫስ (Canvas) መተግበሪያ ግብዓቶች የተማሪ ትምህርት እንዳይቋረጥ ለመደገፍ ጥቅም ላይ ይውላሉ።

## የሠራተኞች ምደባ

እያንዳንዱ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ ሠራተኞችን ይለያል። በአንደኛ ደረጃ ደረጃ ት/ቤት፥ የንባብ ስፔሻሊስቶችን፣ የሰራተኞች ሙያ እድገት አስተማሪዎችን፣ የአስተማሪ ረዳቶችን፣ የክፍል አስተማሪዎችን፣ አስተዳዳሪዎችን እና ሌሎችንም ያካትታል። በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፥ የትምህርት ይዘት አስተማሪዎች በማስተማር ይረዳሉ።

ሁሉም ትምህርት ቤቶች ቀኑን ሙሉ ሁሉም የትምህርት ብሎኮች መሸፈናቸውን ለማረጋገጥ ተዘዋዋሪ የሰራተኞች መርሃ ግብሮችን አዘጋጅተዋል። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሰራተኞች ከበርካታ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን የሚደግፉበትን የክላስተር ሞዴል የመጠቀም አማራጭ አላቸው።

## ልዩ ትምህርት

ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ከሚሰጡት የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች በተጨማሪ ለልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች ዝቅተኛ እና/ወይም ከፍተኛ አጋዥ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች እና አገልግሎቶች IEP ቡድን ውሳኔ መሠረት ተሰጥቷቸዋል።



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# ከአካደሚክ ትምህርት ባሻገር የሚሰጡ አክቲቪቲዎች እና አትሌቲክስ



## በት/ቤቶች መካከል የሚካሄድ አትሌቲክስ

ለኮቪድ-19 ጥንቃቄና ደህንነት ሲባል ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አሠራር ፕሮቶኮሎች እና MCPS የተማሪ-አትሌቲክስ የህክምና አማካሪ ኮሚቴ በሰጠው ሪኮመንዴሽን መሰረት MCPS የትምህርት ቤቶች አትሌቲክስ ፕሮግራም በአካል ማካሄዱን ይቀጥላል። ተማሪ-አትሌቶች፣ የሥራ ባልደረቦች፣ ተመልካቾች እና ሁሉም ባለድርሻ አካላት አሁን ያለውን 'Return to R.A.I.S.E.' ስትራተጂካዊ እቅድ ላይ የተገለጹትን ሂደቶች እና ፕሮቶኮሎች መከተል ይጠበቅባቸዋል። ይህ እቅድ CDC፣ MSDE፣ የሜሪላንድ ፐብሊክ ስኩልስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አትሌቲክስ ማህበር እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ከተላለፉት መመሪያዎች ጋር የተጣጣመ ነው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የአትሌቲክስ በይነመረብ የጤና እና ደህንነት ገጽ ላይ ፕሮግራሙ የሚያከናውናቸውን ስራዎች በተመለከተ የቅርብ ጊዜ መረጃዎችን ያካተተ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ ይሻሻላል።

## ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች እና ስነ- ጥበባት

MCPS ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ ተግባሮች እና የስነ ጥበብ ትምህርት ፕሮግራም ሥራውን በአካል ማከናወን ይቀጥላል።

ተማሪዎች፣ ሰራተኞች እና እንግዶች ከመደበኛ ትምህርት ውጭ በሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሁሉንም ተሳታፊዎች ጤንነትና ደህንነት ለማረጋገጥ ጥንቃቄ የማድረግ ስልቶችን እንዲከተሉ ይበረታታሉ።

ከተማሪ-አትሌት የህክምና አማካሪ ኮሚቴ የተሰጡ ምክሮች እንደአስፈላጊነቱ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ በሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች እና የአርት ፕሮግራሞች ላይ ይተገበራሉ።

MCPS የተማሪ ተሳትፎ ምስክር ወረቀት ለማግኘት በሚያደርጉት ተሣትፎ ተማሪዎች ክሬዲት ያገኛሉ።



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

# 2023-2024 የትምህርት ዓመት የቀን መቁጠሪያ (ካላንደር)

## 2023–2024 **Traditional** School Calendar+ Montgomery County Public Schools

| | |
|---|---|
| **2023** | |
| July 4 | Independence Day—Schools and offices closed |
| August 21, 22, 23, 24, 25 | Professional days for teachers |
| August 28 | First day of school for students |
| September 4 | Labor Day—Schools and offices closed |
| September 22 | Early release day for students |
| September 25 | Non-Instructional Day—No school for students and teachers |
| October 9 | Professional day for all staff; no school for students |
| November 1* | Grading and Planning for the end of term; no school for students |
| November 20 and 21 | Early release days for students |
| November 22 | Systemwide Closure—Schools and offices closed |
| November 23 and 24 | Thanksgiving—Schools and offices closed |
| December 25 | Holiday—Schools and offices closed |
| December 26, 27, 28, 29 | Winter Break—No school for students and teachers |
| December 28 and 29 | Systemwide Closures—Schools and offices closed |
| **2024** | |
| January 1 | New Year's Day—Schools and offices closed |
| January 2 | Non-Instructional Day—No school for students and teachers |
| January 15 | Dr. Martin Luther King, Jr. Day—Schools and offices closed |
| January 29* | Grading and Planning for the end of term; no school for students |
| February 19 | Presidents' Day—Schools and offices closed |
| March 1 | Early release day for students |
| March 25*, 26*, 27, 28 | Spring Break—No school for students and teachers |
| March 27 and 28 | Systemwide Closure—Schools and offices closed |
| March 29 and April 1 | Holidays—Schools and offices closed |
| April 10* | Grading and Planning for the end of term; no school for students |
| April 22* | Professional day for teachers; no school for students |
| May 14 | Primary Election Day—School and offices closed |
| May 27 | Memorial Day—Schools and offices closed |
| June 13 | Last day of school for students; early release day for students |
| June 14* | Grading and Planning for the end of term |
| June 19 | Systemwide Closure—Schools and offices closed |

*If the school year is disrupted by emergencies and schools are closed three or more days, dates identified as possible make-up instructional days include: November 1, 2023; January 29, March 25-26, April 10, April 22, June 14 and June 17–18, 2024.

**+This list of dates does not apply to Arcola and Roscoe R. Nix elementary schools, which will follow the 2023–2024 Innovative School Year Calendar.**

# 2023-2024 የትምህርት ዓመት የቀን መቁጠሪያ (ካላንደር)

**2023–2024 Innovative** School Year Calendar+ Montgomery County Public Schools

| **2023** | |
|---|---|
| July 4 | Independence Day—Schools and offices closed |
| July 3, 4, 5, 6, 7 | No school for students and teachers |
| July 10 | First day of school for students |
| July 28 | Early release day for students |
| August 11 | Early release day for students |
| August 14-18 | No school for students and teachers |
| August 21-25 | No school for students and teachers |
| September 1 | Early release day for students |
| September 4 | Labor Day—Schools and offices closed |
| September 22 | Early release day for students |
| September 25 | Non-Instructional Day—No school for students and teachers |
| October 5 and 6 | Early release days for students |
| October 9 | Professional day for all staff; no school for students |
| October 31 | Early release day for students |
| November 1* | Grading and Planning for the end of term; no school for students |
| November 20 and 21 | Early release days for students |
| November 22 | Systemwide Closure—Schools and offices closed |
| November 23 and 24 | Thanksgiving—Schools and offices closed |
| December 22 | Early release day for students |
| December 25 | Holiday—Schools and offices closed |
| December 26, 27, 28, 29 | Winter Break—No school for students and teachers |
| December 28 and 29 | Systemwide Closures—Schools and offices closed |
| **2024** | |
| January 1 | New Year's Day—Schools and offices closed |
| January 2 | Non-Instructional Day—No school for students and teachers |
| January 15 | Dr. Martin Luther King, Jr. Day—Schools and offices closed |
| January 26 | Early release day for students |
| January 29* | Grading and Planning for the end of term; no school for students |
| February 19 | Presidents' Day—Schools and offices closed |
| March 1 | Early release day for students |
| March 22 | Early release day for students |
| March 25*, 26*, 27, 28 | Spring Break—No school for students and teachers |
| March 27 and 28 | Systemwide Closures—Schools and offices closed |
| March 29 and April 1 | Holidays—Schools and offices closed |
| April 9 | Early release day for students |
| April 10* | Grading and Planning for the end of term; no school for students |
| April 22* | Professional day for teachers; no school for students |
| May 14 | Primary Election Day—Schools and offices closed |
| May 24 | Early release day for students |
| May 27 | Memorial Day—Schools and offices closed |
| June 12 | Early release day for students |
| June 13 | Last day of school for students; early release day for students |
| June 14* | Grading and Planning for the end of term |
| June 19 | Systemwide Closure—Schools and offices closed |

*If the school year is disrupted by emergencies and schools are closed three or more days, dates identified as possible make-up instructional days include: November 1, 2023; January 29, March 25–26, April 10, April 22, June 14, and June 17–18, 2024.

**+This list of dates applies only to Arcola and Roscoe R. Nix elementary schools.**



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*



## ግብረመልስ አቅርብ/Submit Feedback

የእርስዎ አስተያየት እና ግብረመልስ አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ ለምናዘጋጀው እቅድ አስፈላጊ መረጃ ይሰጠናል። ት/ቤቶችን እንደገና ስለመክፈት እቅዳችን ዓመቱን በሙሉ አስተያየት/ግብረመልስ ለመስጠት እባክዎ ይህንን በይነመረብ ይጎብኙ www.mcpssubmitfeedback.org

እባክዎን CDC በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሄ ዕቅድ ማሻሻያ እንደሚደረግበት ይገንዘቡ።